# ምዕራፍ ሦስት

## ሀገራችን

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ውጤቶች**

➢ ተማሪዎች ይህንን ርዕስ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የሀገርን ምንነት ትገልጻላችሁ፣ የኢትዮጵያን መገኛ በአፍሪካ ካርታ ላይ ታመለክታላችሁ::
- የኢትዮጵያን የመሬት ገጽታዎችና ዋና ዋና የውሃ አካላትን በመለየት የአንዳንዶቹን ስም ትጠቅሳላችሁ::
- በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ ብርቅዬ እንስሳትን ስሞች ትጠራላችሁ::
- የኢትዮጵያን ሕዝብ ብዛት በመጥቀስ ሕዝብ ተጠጋግቶና ተበታትኖ የሚኖርባቸውን ክልሎች ትለያላችሁ::
- ፈጣን የሕዝብ ቁጥር መጨመር በዕድገት ላይ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ ትገልጻላችሁ ::
- ግብርናን በሦስት ዓይነት በመክፈል ለሰብል እርሻና ለእንስሳት እርባታ የሚያገለግሉ የታወቁ የእርሻ መሣሪያዎችን ትዘረዝራላችሁ፣ ትጠቀማላችሁ::
- የኢንዱስትሪን ጠቀሜታ በመግለጽና በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋና ኢንዱስትሪዎችን ስሞች በመጥቀስ ኢንዱስትሪዎችን በሦስት ዓይነት ትመድባላችሁ::
- የንግድን ጠቀሜታ በመግለጽ የገቢና ወጪ ንግድ ምሳሌዎችን ትሰጣላችሁ::
- የቱሪዝምን ጠቀሜታ በማስረዳት በኢትዮጵያ ውስጥ የታወቁ የቱሪስት መስህብ ሥፍራዎችን ስም ትጠቅሳላችሁ ::
- የቴክኖሎጂን ጠቀሜታ በማስረዳት በኢትዮጵያ ውስጥ እንዴት ጥቅም እንደሚሰጥ ምሳሌዎችን ትሰጣላችሁ ::
- ቀላል የእጅ (የዕደ ጥበብ) ሥራዎችን ሠርታችሁ ታሳያላችሁ::
- ሳይንሳዊ የምርምር ክህሎቶችን ማለትም:- መመልከትን፣ መመዝገብን፣ መመደብን፣ መጠየቅን፣ መለካትን፣ ከመረጃ በመነሳት ፍንጭ መስጠትን፣ መተንበይን መረጃ መተንተንን፣ ሥዕላዊ መግለጫዎችን በማዘጋጀት መደምደሚያ ላይ መድረስን፣ መረጃ መለዋወጥን፣ መሳይ ቅርጾችን (Models) መሥራትንና አብሮ መሥራትን በተግባር ታሳያላችሁ::

## በምዕራፉ የተካተቱ ይዘቶች:-

3.1 ሀገር ምንድን ናት?
3.2 ዋና ዋና የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴዎች በኢትዮጵያ

## መግቢያ

ተማሪዎች! በሦስተኛ ክፍል የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት ስለከተማችሁ ተፈጥሮአዊ፣ ማኅበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ሁኔታዎች በዝርዝር የተማራችሁትን ታስታውሳላችሁ። በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ስለ ሀገር ምንነት ትማራላችሁ። በተጨማሪም ስለኢትዮጵያ መገኛ፣ አዋሳኝ ሀገሮቿ፣ የኢትዮጵያን የመሬት ገጽታዎች፣ የውሃ አካላት፣ በኢትዮጵያ ስለሚገኙ ብርቅዬ እንስሳት፣ ስለኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥርና በኢትዮጵያ ስለሚገኙ ዋና ዋና የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴዎች በዝርዝር ትገነዘባላችሁ።

## 3.1.ሀገራችን

**ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት**

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ:-

- ሀገር የራሷ ድንበር፣ መንግሥት፣ ሕዝብና ሉአላዊነት ያላት ግዛት መሆኗን ትገልጻላችሁ።
- ከአጎራባች ሀገሮች አንጻር በካርታ ላይ የኢትዮጵያን መገኛ ታመለክታላችሁ።
- የኢትዮጵያን የመሬት ገጽታዎች ከፍተኛ ቦታዎች፣ ዝቅተኛ ቦታዎችና ቆላማና ሸለቋማ በማለት ትለያላችሁ።
- የኢትዮጵያን የመሬት ገጽታዎች ምሳሌዎች ትሰጣላችሁ።
- የኢትዮጵያን ዋና ዋና ወንዞችና ሐይቆች ስሞች ትጠቅሳላችሁ።
- በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ ብርቅዬ እንስሳትን ስሞች ትጠቅሳላችሁ።
- የኢትዮጵያን ሕዝብ ብዛት ትገልጻላችሁ።
- በኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛና ዝቅተኛ የሕዝብ አሠፋፈር ያላቸውን አካባቢዎች ትለያላችሁ።
- ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በልማት ላይ ያለውን ተጽዕኖ ትገልጻላችሁ።

**የንዑስ ርዕስ ይዘቶች**

1. የሀገር ፍቺ (የሀገር ምንነት)
2. ከአጎራባች ሀገሮች አንጻር የኢትዮጵያ መገኛ በካርታ ላይ
3. የመሬት ገጽታዎች
4. የውሃ አካላት
5. በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ ብርቅዬ እንስሳት
6. የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር

## 1. የሀገር ምንነት

**ተግባር 3.1.1** ☛ **የቡድን ውይይት**

**ዓላማ፡-** ስለሀገር ምንነትና መገለጫዎች መግለጽ

**መመሪያ፡-** ከ 3 — 5 በሚደርሱ አባላት ቡድን መሥርታችሁ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።

- በውይይታችሁ የተነሡ ፍሬ ሐሳቦችን ጽፋችሁ በመያዝ ለክፍል መምህራችሁ አቅርቡ።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

- ሀገር ምንድን ናት?
- የሀገር መገለጫ ገጽታዎች ምንድን ናቸው?
- ሀገር ከክልል በምን ይለያል?

ሀገር የራሷ የሆነ ድንበር፣ ማዕከላዊ መንግሥት፣ ሕዝብ፣ ተፈጥሯዊ ገጽታና ሉአላዊ ግዛት አላት።

## 2. የኢትዮጵያ መገኛ

**ተግባር 3.1.2** ☛ **የቡድን ውይይት**

**ዓላማ፡-** የኢትዮጵያ አጎራባች ሀገሮችን በካርታ ላይ መለየት

**መመሪያ፡-** በሥዕል 3.1 የቀረበውን ካርታ በመመልከት የኢትዮጵያ አጎራባች ሀገሮችን ስም በዝርዝር ጻፉ።

- የኢትዮጵያን አጎራባች ሀገሮች ስፋት ከካርታው ላይ በመመልከት ከትንሽ ወደ ትልቅ በቅደም ተከተል አስቀምጡ።

ተማሪዎች! ሀገራችን የት ትገኛለች? በሦስተኛ ክፍል ትምህርታችሁ የከተማችሁን መገኛ ተምራችኋል። በአራተኛ ክፍል ትምህርታችሁ ደግሞ ስለ ሀገራችሁ ኢትዮጵያ መገኛ ትማራላችሁ።

የአንድን ቦታ መገኛ በአንጻራዊና ፍጹማዊ መንገድ መግለጽ እንችላለን። ስለዚህም የኢትዮጵያን መገኛ ለመግለጽ ሁለት መንገዶች እንጠቀማለን። እነርሱም፡-

1. **አንጻራዊ መገኛ**
2. **ፍጹማዊ መገኛ ናቸው።**

## 1. አንጻራዊ መገኛ

ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪካ ቀንድ የምትገኝ ሀገር ናት፡፡ የኢትዮጵያን አንጻራዊ መገኛ ስንገልጽ በሰሜን ኤርትራ፣ በደቡብ ኬንያ፣ በምሥራቅ ጅቡቲና ሶማሊያ በምዕራብ ደግሞ ሱዳንና ደቡብ ሱዳን ያዋስኗታል፡፡

ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪካ የምትገኝ ሉአላዊ ሀገር ናት፡፡ ከኢትዮጵያ በስተሰሜን፣ በስተደቡብ፣ በስተምሥራቅና በስተምዕራብ የተለያዩ ሀገሮች ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ሀገሮችም እንደ ኢትዮጵያ የራሳቸው ዳር ድንበር፣ ማዕከላዊ መንግሥት፣ ተፈጥሯዊ ገጽታና ሕዝብ አላቸው፡፡ ኢትዮጵያ ከአጎራባች ሀገሮቿ ጋር በመከባበርና በሰላም ትኖራለች፡፡


ኢትዮጵያ ስድስት አጎራባች ሀገሮች አሏት፡፡ የሀገሮቹን ስምና መገኛ ከሠንጠረዥ 3.1 ተመልከቱ፡፡

**ሠንጠረዥ 3.1 የኢትዮጵያ አጎራባች ሀገሮች**

| ተ.ቁ | አጎራባች ሀገር | የመገኛ አቅጣጫ |
|---|---|---|
| 1. | ኤርትራ | በስተ ሰሜን |
| 2. | ሱዳን | በስተ ሰሜን ምዕራብ |
| 3. | ደቡብ ሱዳን | በስተ ደቡብ ምዕራብ |
| 4. | የጂቡቲ ሪፐብሊክ | በስተ ምሥራቅ |
| 5. | ሶማሊያ | በስተደቡብ ምሥራቅ |
| 6. | ኬንያ | በስተ ደቡብ |

## 2. ፍጹማዊ መገኛ

ፍጹማዊ መገኛ የአንድን ቦታ ትክክለኛ መገኛ በአኃዝ ልኬት አማካይነት ለመግለጽ የሚያስችል መንገድ ነው፡፡ የኢትዮጵያን ፍጹማዊ መገኛ ስንገልጽ ከ3 ዲግሪ ሰሜን እስከ 12 ዲግሪ ሰሜን እንዲሁም ከ33 ዲግሪ ምሥራቅ እስከ 48 ዲግሪ ምሥራቅ ትገኛለች፡፡ ስለዚህም ኢትዮጵያ ከሰሜን እስከ ደቡባዊ ጫፍ ድረስ 12 ዲግሪ የኬክሮስ (latitudes) ርዝመት ከምሥራቃዊ ጫፍ እስከ ምዕራባዊ ጫፍ 15 ዲግሪ የኬንትሮስ (longitudes) ርዝመት አላት፡፡




ሥዕል 3.1 የኢትዮጵያ አንጻራዊና ፍጹማዊ መገኛ

## የኢትዮጵያ አስተዳደራዊ አወቃቀር

**ተግባር 3.1.3** ☛ የቡድን ውይይት

**ዓላማ:-** የኢትዮጵያ አስተዳደራዊ አወቃቀርን መለየት

**መመሪያ:-** የኢትዮጵያ አስተዳደራዊ አወቃቀር በምን በምን መሠረት ላይ እንደተዋቀረ በዝርዝር ጻፉ፡፡

- የኢትዮጵያን ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታትና የከተማ አስተዳደሮችን ዘርዝሩ፡፡

የሀገራችን ኢትዮጵያ መጠሪያ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ በመባል ይታወቃል፡፡ ሀገራችን የሕዝብ አሠፋፈርን፣ ቋንቋን፣ ባሕልንና የሕዝብ ፍላጎትን መሠረት ባደረገ አስተዳደራዊ ክልሎች ተደራጅታለች፡፡

ስለዚህም በሀገራችን ዘጠኝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታትና ሁለት የከተማ አስተዳደሮች በፈቃደኝነት ተባብረው የመሠረቷት ሀገር ናት፡፡

## ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታትና የከተማ አስተዳደሮች

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ በክልሎች የተመሠረተ ነው፡፡ እያንዳንዱ ክልል የራሱ ርዕሰ ከተማ አለው፡፡ የክልሎቹን ስምና ርዕሰ ከተማቸውን ከሚቀጥለው ሠንጠረዥ ተመልከቱ፡፡

## ሠንጠረዥ 3.2 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታትና የከተማ አስተዳደሮች

| ክልል | የክልሉ ስም | ርዕሰ ከተማ |
|---|---|---|
| 1 | የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት | መቐሌ |
| 2 | የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት | ሰመራ |
| 3 | የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት | ባሕርዳር |
| 4 | የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት | ፊንፊኔ |
| 5 | የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት | ጅጅጋ |
| 6 | የቤኒሻንጉል ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት | አሶሳ |
| 7 | የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት | ሀዋሳ |
| 8 | የሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት | ሐረር |
| 9 | የጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት | ጋምቤላ |

| | የከተማ አስተዳደር | ርዕሰ ከተማ |
|---|---|---|
| 1 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር | አዲስ አበባ |
| 2 | የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር | ድሬዳዋ |

ሀገሮች ከሚኖሯቸው ግንኙነቶች በጣም የሚታወቁት ምጣኔ ሀብታዊና ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶች ናቸው፡፡ ምጣኔ ሀብታዊ ግንኙነት በንግድና በቱሪዝም ይገለጻል፡፡ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ደግሞ ሀገሮች እርስ በርሳቸው በመከባበር በመልዕክተኞች አማካይነት ውይይት በማድረግ ማዕከላዊ መንግሥታት ተከባብረውና ሉአላዊነታቸውን ጠብቀው የሚኖሩበት የግንኙነት ስልት ነው፡፡ ይህን ግንኙነት ለማጠናከር ሀገሮች ሙሉ ሥልጣን ያለው መልእክተኛ ያስቀምጣሉ፡፡ ይህ መልእክተኛ በተላከበት ሀገር ሀገሩን ወክሎ፣ መኖሪያው ታውቆ የሚገኝ ባለሙሉ ሥልጣንና የሀገርን ጥቅም የሚያስከብር የሀገር ተወካይ ነው፡፡

## 3. የኢትዮጵያ የመሬት ገጽታዎች

**ተግባር 3.1.4** ☛ **የቡድን ውይይት**


**ዓላማ፡-** የኢትዮጵያ የመሬት ገጽታዎችን ከካርታ ላይ መለየት

**መመሪያ፡-** ከ3-5 በሚደርሱ አባላት ቡድን መሥርታችሁ ተወያዩ፡፡

- የተወያያችሁበትን ነጥብ በተወካያችሁ አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. በኢትዮጵያ ከፍተኛ ቦታዎች የሚገኙት በየት አካባቢ ነው?
2. በኢትዮጵያ ዝቅተኛ ሥፍራዎች የሚገኙት በየት አካባቢ ነው?




*ሥዕል 3.2 የኢትዮጵያ የመሬት ገጽታዎች*

ኢትዮጵያ ልዩ ልዩ የመሬት ገጽታዎች አሏት፡፡ እነዚህ የመሬት ገጽታዎች በጥቅሉ ከፍተኛ ቦታዎች፣ ዝቅተኛ ቦታዎችና ሸለቆዎች በመባል ይታወቃሉ፡፡ እነዚህን ሥፍራዎች በሥዕል 3.2 እንደተመለከቱት በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ይገኛሉ፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ ሥፍራዎች በሰሜን ምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብና በደቡብ ምሥራቅ ይገኛሉ፡፡ የሚከተለው ሠንጠረዥ ከፍተኛ ቦታዎችን (ተራሮችን) ያመለክታል፡፡

## ሰንጠረዥ 3.3. የኢትዮጵያ ከፍተኛ ሥፍራዎች

| ተ.ቁ | የተራራው ስም | ከፍታ በሜትር | የሚገኝበት ክልል |
|---|---|---|---|
| 1. | ራስ ደጀን | 4620 | አማራ |
| 2. | ላገዳ | 4532 | አማራ |
| 3. | አናሎ | 4480 | አማራ |
| 4. | ወንበራ | 4472 | አማራ |
| 5. | አባያሬድ | 4460 | አማራ |
| 6. | ጣፊው ለዘር | 4456 | አማራ |
| 7. | ቧሂት | 4437 | አማራ |
| 8. | ሙሰሪያ | 4360 | አማራ |
| 9. | ካራ | 4307 | ኦሮሚያ |
| 10. | ባቱ | 4300 | ኦሮሚያ |

***ምንጭ፡-*** የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ /1999፡6/ ዓመታዊ የስታቲክስ መጽሔት፡፡ አዲስ አበባ፡፡

**ተግባር 3.1.5** ☛ ***በግል የሚከናወን ተግባር***

**ዓላማ፡-** በኢትዮጵያ የሚገኙ ከፍተኛ ቦታዎችን ማወዳደር

**መረጃ፡-** ሠንጠረዥ 3.3

**የማነጻጸሪያ ጥያቄዎች**

- ከኢትዮጵያ ከፍተኛ ቦታዎች ከፍተኛው ተራራ የት ይገኛል ? ከፍታውስ ስንት ሜትር ነው?
- በኢትዮጵያ ከፍተኛ ቦታዎች በብዛት የሚገኙት በየትኛው ክልል ነው?

የኢትዮጵያ ከፍተኛ ቦታዎች በአማካይ ከፍታቸው ከባሕር ጠለል በላይ 1000 ሜትርና ከዚያ በላይ ነው፡፡ ስለዚህ 1000 ሜትር የከፍተኛ ሥፍራና የዝቅተኛ ቦታ መለያ የከፍታ ልኬት ነው፡፡

በኢትዮጵያ ዝቅተኛ ቦታዎችም ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ዝቅተኛ ቦታዎች በምዕራብ፣ በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ ይገኛሉ፡፡

**ተግባር 3.1.6** ☛ **የቡድን ሥራ**

**ዓላማ፡-** በኢትዮጵያ የሚገኙ ዝቅተኛ ሥፍራዎችን መለየት

**መመሪያ፡-** ከ3-5 አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት ከካርታ ላይ የኢትዮጵያን ዝቅተኛ ቦታዎች መለየት

**የትኩረት ጥያቄዎች**

- በኢትዮጵያ ዝቅተኛ ቦታዎች በስፋት የሚገኙት በየት አካባቢ ነው?
- የምዕራብ፣ የደቡብና የደቡብ ምሥራቅ ዝቅተኛ ቦታዎች የሚያዋስኗቸውን ቦታዎች ዘርዝሩ፡፡

በምዕራብ የሚገኙት ዝቅተኛ ቦታዎች የኢትዮጵያን፣ የሱዳንንና የደቡብ ሱዳንን ድንበር ያካልላሉ፡፡ የምዕራብ ኢትዮጵያ ዝቅተኛ ሥፍራዎች ጠባብ ሆነው ረጅም ሥፍራ ይሸፍናሉ፡፡ በስተደቡብ የሚገኙት ዝቅተኛ ቦታዎች ደግሞ የኢትዮጵያንና የኬንያን የጋራ ድንበሮች ያዋስናሉ፡፡ የደቡብ ምሥራቅ ዝቅተኛ ቦታዎች የኢትዮጵያንና የሶማሊያን የጋራ ድንበር የሚያካልሉ ሲሆን ሰፊ ሥፍራ ያጠቃልላሉ፡፡ /ምስል 3.2 ተመልከቱ/

የምዕራብ ዝቅተኛ ቦታዎችን፣ የተከዜ ሰቲት ዝቅተኛ ሥፍራን፣ የአባይ ዲንደር ዝቅተኛ ሥፍራንና የባሮ ዝቅተኛ ሥፍራን ያጠቃልላሉ፡፡ የደቡብ ምሥራቅ ዝቅተኛ ቦታዎች የኦጋዴንን ዝቅተኛ ሥፍራዎች ያካትታሉ፡፡

**ተግባር 3.1.7** ☛ **የጥንድ ሥራ**

**ዓላማ፡-** የኢትዮጵያን ስምጥ ሸለቆ ለይቶ ማሳየት

**የትኩረት ጥያቄዎች**

- የኢትዮጵያን ስምጥ ሸለቆ መነሻና መድረሻ ጫፍ ግለጹ፡፡
- የኢትዮጵያን ስምጥ ሸለቆ የሚያዋስኑ የመሬት ገጽታዎችን በንድፍ ካርታ ላይ አመልክቱ፡፡
- በስምጥ ሸለቆ ውስጥ የሚገኙ የወንዝ ተፋሰሶችን ዘርዝሩ፡፡

የኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ ከሰሜን ምሥራቅ ወደ ደቡብ ምዕራብ የሚዘረጋ የመሬት ገጽታ ነው፡፡ ሸለቆ ዝቅተኛ ሥፍራ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ በዘመናት ውስጥ የአካባቢው የመሬት ገጽ ሰርጎ በመግባቱ ምክንያት የተፈጠረ የመሬት ገጽ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ ወንዞችና ሐይቆች ይገኛሉ፡፡ ከወንዞቹ ታዋቂው አዋሽ ነው፡፡ በስምጥ ሸለቆ የሚገኙ ሐይቆች በርካታ ሲሆኑ ላንጋኖ፣ ዝዋይ፣ ሻላና አብያታ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

በኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ ውስጥ ለዘመናት ሲፈሱ የኖሩ የወንዝ ተፋሰሶች አሉ፡፡ ለምሳሌ የዓባይ ወንዝ ሸለቆን፣ የባሮ ወንዝ ሸለቆንና የገናሌ ወንዝ ሸለቆን መጥቀስ ይቻላል፡፡

በኢትዮጵያ የተለያዩ ቆላማ ሥፍራዎች ይገኛሉ፡፡ ቆላማ ሥፍራዎች ከባሕር ጠለል በላይ ከፍታቸው ከ500-1500 ሜትር የሚደርሱትን ቦታዎች በሙሉ ያጠቃልላሉ፡፡ ቆላማ ሥፍራዎች የሚገኙት በዝቅተኛ ቦታዎች ነው፡፡

## መልመጃ 3.1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

1. ሀገር ምንድን ናት?
2. የኢትዮጵያን አጎራባች ሀገሮች ስም ዘርዝሩ?
3. የሀገሮች ግንኙነቶች ዋና ዋና መገለጫዎች ምንድን ናቸው?
4. የኢትዮጵያን ከፍተኛና ዝቅተኛ የመሬት ገጽታዎች ዘርዝሩ፡፡
5. የኢትዮጵያን ስምጥ ሸለቆ አቀማመጥ አቅጣጫን ግለጹ፡፡

## 4. የውሃ አካላት

ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪካ ከሚገኙ ሀገሮች በውኃ ሀብት ቀዳሚውን ሥፍራ የያዘች ሀገር ናት፡፡ በሀገራችን የተለያዩ ወንዞችና ሐይቆች ይገኛሉ፡፡

### ሀ. ወንዞች

በሀገራችን የሚገኙ ወንዞች ከከፍተኛ ቦታዎች ስለሚነሡ ከፍተኛ ፍጥነት አላቸው፡፡ በተጨማሪም በክረምትና በበጋ ወቅት የውሃ መጠናቸው የተለያየ ነው፡፡ በዚህ የተነሣ አብዛኛዎቹ በኢትዮጵያ የሚገኙ ወንዞች ለኃይል ማመንጫነት እንጂ ለመጓጓዣነት አያገለግሉም፡፡

የሀገራችን ወንዞች ወደተለያዩ አቅጣጫዎች ይፈሳሉ፡፡ ለምሳሌ ዓባይ፣ የተከዜና የባሮ ወንዞች ከሰሜን ምዕራብ ከፍተኛ ቦታዎች በመነሣት ወደ ምዕራብ ዝቅተኛ ሥፍራዎች ይፈሳሉ፡፡ የጊቤ ወንዝ ደግሞ ከደቡብ ከፍተኛ ቦታዎች በመነሣት ወደ ደቡብ ዝቅተኛ ሥፍራዎች ይፈሳል፡፡

ከደቡብ ምሥራቅ ከፍተኛ ቦታዎች የሚነሡ ወንዞችም ወደ ደቡብ ምሥራቅ ዝቅተኛ ሥፍራዎች ይፈሳሉ፡፡ የአዋሽ ወንዝ ደግሞ ከምዕራብ ከፍተኛ ቦታዎች በመነሣት ወደ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ በመፈሰስ ወደ ሰሜን ምሥራቅ አቅጣጫ ይጓዛል፡፡ ይህ ወንዝ የስምጥ ሸለቆ አካባቢን በስፋት ይሸፍናል፡፡
/ምስል 3.3 ተመልከቱ/፡፡




ሥዕል 3.3 ዋና ዋና የኢትዮጵያ ወንዞች

**ተግባር 3.1.8** ☛ **የቡድን ሥራ**

**ዓላማ፡-** ወንዞች የሚፈሱባቸውን አቅጣጫዎች መለየት

**መመሪያ፡-** ከ3-5 በሚደርሱ አባላት ቡድን መሥርታችሁ የሀገራችን ወንዞች የሚነሡበትንና የሚፈሱበትን አቅጣጫዎች በንድፍ ካርታ ላይ አመልክቱ፡፡

**የመወያያ ጥያቄዎች**

- ከደቡብ ምሥራቅ ከፍተኛ ቦታዎች ተነሥተው የሚፈሱ ወንዞችን ስም ዘርዝሩ፡፡
- ከሰሜን ምዕራብ ከፍተኛ ቦታዎች የሚነሡ ወንዞች ለምን ወደ ምዕራብ ዝቅተኛ ሥፍራዎች ይፈሳሉ?
- ከሰሜን ምዕራብ ከፍተኛ ቦታዎች ከሚነሡ ወንዞች ሦስቱን ጥቀሱ፡፡


በኢትዮጵያ የሚገኙ ወንዞች የፍሰት መጠንና የሚሸፍኑት አካባቢ ተመሳሳይ አይደለም፡፡

### ሰንጠረዥ 3.4 የኢትዮጵያ ወንዞች መነሻና የፍሰት አቅጣጫ

| ተ.ቁ | ወንዝ | መነሻ ከፍተኛ ሥፍራ | የፍሰት አቅጣጫ |
|---|---|---|---|
| 1. | ዓባይ | ሰሜን ምዕራብ ከፍተኛ ቦታዎች | ምዕራብ |
| 2. | ተከዜ | ሰሜን ምዕራብ ከፍተኛ ቦታዎች | ምዕራብ |
| 3. | ባሮ | ሰሜን ምዕራብ ከፍተኛ ቦታዎች | ምዕራብ |
| 4. | ዋቢ ሸበሌ | ደቡብ ምሥራቅ ከፍተኛ ቦታዎች | ምሥራቅ |
| 5. | ገናሌ | ደቡብ ምሥራቅ ከፍተኛ ቦታዎች | ምዕራብ |
| 6. | ጊቤ | ደቡብ ምዕራብ ከፍተኛ ቦታዎች | ደቡብ |
| 7. | አዋሽ | ደቡብ ምዕራብ ከፍተኛ ቦታዎች | ሰሜን ምሥራቅ |

### ለ. ሐይቆች

በሀገራችን ሐይቆች በስምጥ ሸለቆና በከፍተኛ ሥፍራዎች ይገኛሉ፡፡ በከፍተኛ ሥፍራዎች የሚገኙ ሐይቆች አፈጣጠር የተለያየ ቢሆንም በጥቅሉ የከፍተኛ ሥፍራ ሐይቆች ይባላሉ፡፡ የዝቅተኛ ሥፍራ ሐይቆች ደግሞ የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች በመባል ይታወቃሉ፡፡ የጣና ሐይቅ በስፋት ትልቁ ሐይቅ ነው፡፡ ሻላ ከፍተኛ ጥልቀት ያለው ሐይቅ ሲሆን ዝዋይ ደግሞ በጥልቀት ዝቅተኛውን ሥፍራ ይይዛል፡፡ የሚከተለው ምስል የስምጥ ሸለቆ ሐይቆችን መገኛ ያሳያል፡፡




ሥዕል 3.4 የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች



ሥዕል 3.5 ጣና ሐይቅ

## ሰንጠረዥ 3.5 የኢትዮጵያ ሐይቆች

| ተ.ቁ | ሐይቅ | መገኛ |
|---|---|---|
| 1. | ጣና | ከፍተኛ ሥፍራ |
| 2. | አባያ | ስምጥ ሸለቆ |
| 3. | ጫሞ | ስምጥ ሸለቆ |
| 4. | ዝዋይ | ስምጥ ሸለቆ |
| 5. | ሻላ | ስምጥ ሸለቆ |
| 6. | ሐዋሳ | ስምጥ ሸለቆ |
| 7. | አቢያታ | ስምጥ ሸለቆ |
| 8. | ቢሾፍቱ | ስምጥ ሸለቆ |
| 9. | ባቦ ጋያ | ስምጥ ሸለቆ |
| 10. | አርሰዲ | ስምጥ ሸለቆ |
| 11. | ወንጪ | ከፍተኛ ሥፍራ |
| 12. | ሐይቅ | ከፍተኛ ሥፍራ |
| 13. | አሸንጌ | ከፍተኛ ሥፍራ |

**ተግባር 3.1.9** ☛ **በግል የሚከናወን ተግባር**

**ዓላማ**:- የሐይቆችን መገኛ በካርታ ላይ ሠርቶ ማሳየት

**መረጃ**:- የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች

**መረጃ መሣሪያ**:- አትላስ

**የአሠራር መመሪያ**

የሚከተለውን የግል ሥራ በመሥራት ለክፍል መምህራችሁ አቅርቡ።

- ካርታውን ከአትላስ ላይ በስስ ወረቀት አማካይነት ማንሣት
- ስስ ወረቀቱን ነጭ ዝርግ ወረቀት ላይ በማድረግ መስመሩን ተከትሎ ማድመቅ።
- ሐይቆቹን በትክክለኛ ቦታቸው ላይ ማሳየት
- ሐይቆቹ የሚይዙትን ሥፍራ በሰማያዊ ቀለም መቀባት
- ለሐይቆቹ የቁጥር ስያሜ መስጠት
- ማውጫ በማዘጋጀት በቁጥሮቹ አንጻር የሐይቆቹን ስሞች መጻፍ

ካርታውን ለመሥራት የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች

- ስስ ወረቀት
- ነጭ ዝርግ ወረቀት
- እርሳስ
- ላጲስ
- ጥቁር እስክሪብቶ
- ሰማያዊ ቀለም

## 5. በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ ብርቅዬ የዱር እንስሳት

በኢትዮጵያ በርካታ የዱር እንስሳት ይገኛሉ። እነዚህ እንስሳት በተለያዩ የተፈጥሮ አካባቢዎች ይገኛሉ።

አንዳንድ እንስሳት ቁጥራቸው በጣም አነስተኛ ከመሆኑም በላይ የሚኖሩበትም ሥፍራ ውስን ነው። እንስሳቱ በሁሉም አካባቢ ሊገኙ ባለመቻላቸው ብርቅዬ በሚል ስያሜ ይታወቃሉ።


ዋልያ


ኒያላ (የደጋ አጋዘን)


ቀይ ቀበሮ



የምኒሊክ ድኩላ



ጭላዳ ዝንጀሮ



ቆርኬ

ሥዕል 3.6 በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ ብርቅዬ የዱር እንስሳት

ሰንጠረዥ 3.6 ብርቅዬ የዱር እንስሳትና መገኛቸው

| ተ.ቁ | ብርቅዬ እንስሳ | የብርቅዬ እንሰሳው ዓይነት | መገኛ | ብሔራዊ ክልል |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ዋልያ | ሣር በል | ስሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ | አማራ |
| 2. | ኒያላ /የደጋ አጋዘን/ | ሣር በል | ባሌ ብሔራዊ ፓርክ | ኦሮሚያ |
| 3. | ቀይ ቀበሮ | ሥጋ በል | ስሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ<br>ባሌ ብሔራዊ ፓርክ | አማራ<br>ኦሮሚያ |
| 4. | ጭላዳ ዝንጀሮ | ቅጠላ ቅጠል በል | ስሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ | አማራ |
| 5. | የስዌን ቆርኬ | ሣር በል | ሰንቀሌ የዱር እንስሳት መከላከያና መጠበቂያ | ኦሮሚያ |
| 6. | የምኒልክ ዱኩላ | ሣር በል | ባሌ ብሔራዊ ፓርክ<br>ቁኒ ሙክታር የዱር እንስሳት መከለያና መጠበቂያ<br>ስሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ | ኦሮሚያ<br>አማራ |

**ተግባር 3.1.10** ☛ *የቡድን ሥራ*

**ዓላማ፡-** የብርቅዬ ዱር እንስሳትን ምስሎች ለእይታ ማብቃት

**መመሪያ**፡- ከ3-5 በሚደርሱ አባላት ቡድን መሥርታችሁ የብርቅዬ ዱር እንስሳትን ምስሎች አሰባስባችሁ በወፍራም ወረቀት ላይ በመለጠፍ ለእይታ ዝግጁ አድርጉ፡፡

**የምስል መገኛዎች**

- ቴምብሮች
- ጋዜጦች
- መጽሔቶች
- ቀን መቁጠሪያዎች

**ለእይታ የሚበቃውን ቻርት ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉ ቁሳቁስ**

- ሥዕሎች
- ወፍራም ወረቀት
- ግልጽ ፕላስተር
- ማጣበቂያ
- እርሳስ
- ማስመሪያ
- መቀስ
- ለምስሎቹ መሸፈኛ የሚውል ላስቲክ

**የተግባር እንቅስቃሴ**

- በጥንድ ሆኖ ምስሎች መሰብሰብ፡፡
- ከተሰበሰቡት ምስሎች የተሻሉትን መምረጥ፡፡
- ወፍራም ወረቀት ማዘጋጀት፡፡
- እያንዳንዱ የብርቅዬ እንስሳ ሥዕል የሚለጠፍበትን ቦታ በማስመሪያ መወሰን፡፡
- የእያንዳንዱን ሥዕል መለጠፊያ ሥፍራ ከልኬቱ ጋር ማጣጣም፡፡
- ሥዕሎቹ ከተለጠፉ በኋላ በጥንቃቄ በላስቲክ መሸፈን፡፡

  በመጨረሻም ለሥዕሎቹ ማንጠልጠያ አዘጋጅቶ መስቀል ወይም በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ መለጠፍ፡፡

## መልመጃ 3.2

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ**

1. በኢትዮጵያ የሚገኙ ከፍተኛ ተራራዎችን ስያሜና የሚገኙበትን ቦታ ዘርዝሩ፡፡
2. የወንዞችን የአፈሳሰስ አቅጣጫ የሚወስነው ምንድን ነው?
3. ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ከሚፈሱ የኢትዮጵያ ወንዞች ሁለቱን ዘርዝሩ?
4. በስምጥ ሸለቆ ከሚገኙ ሐይቆች አራቱን ዘርዝሩ?
5. ከከፍተኛ ሥፍራ ሐይቆች ሁለቱን ጥቀሱ?
6. በሀገራችን የሚገኙትን ብርቅዬ የዱር እንስሳት ስም ዘርዝሩ፡፡

## 6. የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር

### ሀ. የሕዝብ ብዛት

የኢትዮጵያን ሕዝብ ብዛት ለማወቅ በተለያዩ ጊዜያት የሕዝብ ቆጠራ ተካሂዷል፡፡ በተጨማሪም በተለያዩ ጊዜያት የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ትንበያ ተሠርቷል፡፡ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ትንበያ የሚካሄደው የሕዝብ ቆጠራ በማይካሄድበት ጊዜ ነው፡፡ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ትንበያ የሚካሄደው ቀደም ሲል በተካሄደው የሕዝብ ቆጠራ ላይ በመመሥረት ነው፡፡ በ1999 ዓ.ም. በተካሄደው የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት 73,918,505 ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በመጨመር ላይ ይገኛል፡፡ በ2000 ዓ.ም በተደረገ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ትንበያ መሠረት የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት ከ80 ሚሊዮን በላይ ደርሷል፡፡

### ለ. የሕዝብ ሥርጭት

የሕዝብ ሥርጭት ሰዎች በተለያዩ ሥፍራዎች ሠፍረው የሚገኙበትን ሁኔታ የሚገልጽ ነው፡፡ የሰዎች የአሠፋፈር ሁኔታ በሁሉም ቦታ አንድ ዓይነት አይደለም፡፡ በአንዳንድ አካባቢ የተጠጋጋ ሲሆን፣ በሌላው አካባቢ መካከለኛ፣ በቀረው አካባቢ ደግሞ የተበታተነ ሊሆን ይችላል፡፡

ሰንጠረዥ 3.7. በ1999 ዓ.ም የሕዝብ ቆጠራ መሠረት የኢትዮጵያ ሕዝብ ሥርጭት በክልል

| ክልል | የሕዝብ ብዛት | በመቶኛ % |
|---|---|---|
| ትግራይ | 3,314,456 | 5.8 |
| አፋር | 1,411,092 | 1.9 |
| አማራ | 17,214,056 | 23.3 |
| ኦሮሚያ | 27,158,471 | 36.7 |
| ሶማሌ | 4,439,147 | 6.0 |
| ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | 670,847 | 0.9 |
| ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች | 15,042,531 | 20.4 |
| ጋምቤላ | 306,916 | 0.4 |
| ሐረሪ | 83,344 | 0.2 |
| አዲስ አበባ | 2,738,248 | 3.7 |
| ድሬዳዋ | 342,827 | 0.5 |
| ልዩ አቆጣጠር | 96,570 | 0.1 |
| ጠቅላላ የሕዝብ ብዛት | 73,918,505 | 100.0 |

**ተግባር 3.1.11** ☛ ***የጥንድ ሥራ***

**ዓላማ:-** ሕዝብ በብዛት የሚገኝባቸውን ክልሎች በደረጃ ማስቀመጥ

**መመሪያ:-** ሁለት ሁለት በመሆን ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ::

**ጥያቄዎች**

- በሕዝብ ብዛት ከፍተኛውን ሥፍራ የያዘው የትኛው ክልል ነው?
- በሕዝብ ብዛታቸው በሁለተኛና በሦስተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙት ክልሎች የትኞቹ ናቸው?
- በሕዝብ ቁጥር አነስተኛው ክልል የትኛው ነው?
- ከጠቅላላው የኢትዮጵያ ሕዝብ 80.4 በመቶ ያህሉን የያዙት ክልሎች የትኞቹ ናቸው?

በኢትዮጵያ ሕዝብ ተጠጋግቶና ተበታትኖ የሚኖርባቸው አካባቢዎች አሉ:: እነዚህ አካባቢዎች በተለያዩ ክልሎች ውስጥ የሚገኙ ዞኖች ናቸው::

**ሰንጠረዥ 3.8. እ.ኤ.አ. በ2009 በተሰበሰበ መረጃ ከፍተኛ የሕዝብ ጥግግት የተሰተዋለባቸው አካባቢዎች**

| ተ.ቁ | ዞን | የሕዝብ ጥግግት በ1ካሬ ኪሎ ሜትር | ክልል |
|---|---|---|---|
| 1 | ጌዲኦ | 773 | ደቡብ ሕዝቦች |
| 2 | ከምባታ ጠምባሮ | 536 | ደቡብ ሕዝቦች |
| 3 | ሲዳማ | 483 | ደቡብ ሕዝቦች |
| 4 | ወላይታ | 386 | ደቡብ ሕዝቦች |
| 5 | ሃድያ | 368 | ደቡብ ሕዝቦች |
| 6 | ጉራጌ | 231 | ደቡብ ሕዝቦች |
| 7 | ምዕራብ አርሲ | 184 | ኦሮሚያ |
| 8 | ምሥራቅ ሸዋ | 178 | ኦሮሚያ |
| 9 | ጅማ | 176 | ኦሮሚያ |
| 10 | ምሥራቅ ሐረርጌ | 167 | ኦሮሚያ |

የሕዝብ ጥግግት ማለት በአንድ በታወቀ አካባቢ የሚገኝ ሕዝብ ከሚኖርበት ሥፍራ ጋር ተነጻጽሮ የሕዝቡ ቁጥር በሥፍራው ስፋት ተከፍሎ የሚገኘው ውጤት ነው::

## መልመጃ 3.3

ሰንጠረዥ 3.8 በመመልከት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ

1. ከፍተኛ የሕዝብ ጥግግት ያለው የትኛው ዞን ነው?
2. ከፍተኛ የሕዝብ ጥግግት የሚታይባቸው ዞኖች በየትኞቹ ናቸው?
3. የሕዝብ ጥግግታቸው በካሬ ኪሎ ሜትር ከ190 ሰዎች በላይ ያላቸውን ዞኖች ዘርዝሩ፡፡
4. የሕዝብ ጥግግታቸው በካሬ ኪሎ ሜትር ከ360 በላይ የሆኑ ዞኖችን ዘርዝሩ፡፡
5. በሲዳማ ዞንና በጉራጌ ዞን መካከል የሚታየው የሕዝብ ጥግግት ልዩነት ምን ያህል ነው?

ሰንጠረዥ 3.9. እ.ኤ.አ. በ2009 በተሰበሰበ መረጃ አነስተኛ የሕዝብ ጥግግት ያላቸው ዞኖች

| ተ.ቁ | ዞን | የሕዝብ ጥግግት በ1ካሬ ኪሎ ሜትር | ክልል |
|---|---|---|---|
| 1 | አኙዋክ | 6 ሰዎች | ጋምቤላ |
| 2 | መተከል | 10 ሰዎች | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ |
| 3 | ከማሺ | 11 ሰዎች | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ |
| 4 | አፋር/ዞን1/ | 15 ሰዎች | አፋር |
| 5 | ኢታንግ ልዩ ዞን | 19 ሰዎች | ጋምቤላ |
| 6 | አፋር /ዞን2/ | 21 ሰዎች | አፋር |
| 7 | አሶሳ | 23 ሰዎች | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ |
| 8 | ዋርዴር | ከ 6- 25 ሰዎች | ሶማሌ |
| 9 | ቆራሄ | | ሶማሌ |
| 10 | ፊቅ | | ሶማሌ |

## መልመጃ 3.4

ሰንጠረዥ 3.8 በመመልከት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ

1. አነስተኛ የሕዝብ ጥግግት ያለባቸው ዞኖች ሲወዳደሩ ዝቅተኛ ጥግግት የሚታየው በየትኛው ዞን ነው?
2. በ1 ካሬ ኪሎ ሜትር ከ 10 ሰዎች በታች የሚገኙባቸው ዞኖች የትኞቹ ናቸው?
3. በአፋርና በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት የሚታየው የሕዝብ ጥግግት ምን ያህል ነው?

በከተማና በገጠር ያለው የሕዝብ አሠፋፈር ሥርጭት የተለያየ ነው፡፡ በኢትዮጵያ 84 በመቶ ያህል ሕዝብ የሚኖረው በገጠር ሲሆን 16 በመቶ የሚደርሰው ሕዝብ ደግሞ በከተማ ይኖራል፡፡

ለምሳሌ በ2003 ዓ.ም. በተደረገ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ትንበያ መሠረት በገጠር የሚኖረው ሕዝብ ብዛት 68,350,472 ሲሆን በከተማ የሚኖረው ደግሞ 17,600,000 ነበር፡፡

**ሰንጠረዥ 3.10. በ1999 ዓ.ም በተደረገው የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ ውጤት የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት ሥርጭት በጾታ**

| ተ.ቁ | ክልል | ጾታ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | | ሴት | |
| | | ቁጥር | መቶኛ | ቁጥር | መቶኛ |
| 1 | ትግራይ | 2,124,853 | 49.2 | 2,189,603 | 50.8 |
| 2 | አፋር | 786,338 | 55.7 | 624,754 | 44.3 |
| 3 | አማራ | 8,636,875 | 50.2 | 8,577,181 | 49.8 |
| 4 | ኦሮሚያ | 13,676,159 | 50.4 | 13,482,312 | 49.6 |
| 5 | ሶማሌ | 2,468,784 | 55.6 | 1,970,363 | 44.4 |
| 6 | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | 340,378 | 50.7 | 330,469 | 49.3 |
| 7 | ደቡብ ሕዝቦች | 7,482,051 | 49.7 | 7,560,480 | 50.3 |
| 8 | ጋምቤላ | 159,679 | 52.0 | 147,237 | 48.0 |
| 9 | ሐረሪ | 92,258 | 50.3 | 91,086 | 49.7 |
| 10 | አዲስ አበባ | 1,304,518 | 47.6 | 1,433,730 | 52.4 |
| 11 | ድሬደዋ | 171,930 | 50.2 | 170,897 | 49.8 |
| 12 | ልዩ አቆጣጠር | 52,834 | 54.7 | 43,736 | 45.3 |
| ጠቅላላ የሕዝብ ብዛት | | 37,296,657 | 50.5 | 36,621,848 | 49.5 |

## መልመጃ 3.5

**በሰንጠረዥ 3.9 መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡**

1. የወንዶች ቁጥር ከሴቶቹ ቁጥር የሚበልጥባቸው ወይንም የሚበዛባቸው ክልሎች የትኞቹ ናቸው?
2. የሴቶች ቁጥር ከወንዶች ቁጥር የሚበልጡባቸውን ክልሎች ዘርዝሩ፡፡
3. በአጠቃላይ በሰንጠረዡ መሠረት በኢትዮጵያ የሕዝብ ቤት ቆጠራ በተደረገበት ዘመን የሴቶች ብዛት በመቶኛ ምን ያህል ነበር?

የሕዝብ ብዛት በዕድሜ ምድብም ይታወቃል፡፡ የሕዝብና የቤቶች ቆጠራና የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ትንበያ ሲካሄድ የሕዝብ ቁጥር በዕድሜ ምድብ ተለይቶ ይቀመጣል፡፡

ሠንጠረዥ 3.11 የኢትዮጵያ ሕዝብ ሥርጭት በዕድሜ ጥንቅር

| ዘመን | የሕዝብ ብዛት በሚሊየን | የኢትዮጵያ ሕዝብ ሥርጭት በዕድሜ በመቶኛ ሲገለጽ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ከ15 ዓመት በታች | ከ15 - 64 ዓመት | 65 ና ከዚያ በላይ | ድምር |
| 1976 | 41.1 | 48.1 | 47.1 | 4.8 | 100 |
| 1986 | 53.4 | 45.4 | 51.4 | 3.2 | 100 |
| 1999 | 73.9 | 45.0 | 51.8 | 3.2 | 100 |
| 2002 | 79.0 | 44.0 | 53.0 | 3.0 | 100 |

## መልመጃ 3.6

1. በሠንጠረዡ መሠረት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች የትኞቹ ናቸው?
2. አነስተኛ ቁጥር ያላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎችስ የትኞቹ ናቸው?

### ሐ. የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በልማት ላይ ያለው ተጽእኖ

የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ከመሬት ቆዳ ስፋት ጋር የተመጣጠነ መሆን አለበት፡፡ የሕዝብ ቁጥር አንድ አካባቢ ሊይዘው ከሚገባው የሕዝብ ብዛት ከበለጠ በምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴና በማኅበራዊ አገልግሎቶች ላይ ተጽእኖ ይፈጥራል፡፡ **ለምሳሌ፡-** በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ሲጨምር ለእርሻ የተያዘው ሥፍራ እየጠበበ ይሄዳል፡፡ ይህ ሁኔታ በምግብ አቅርቦት ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡ በአጠቃላይ ከእርሻ የሚገኘው የምግብ እህል አነስተኛ ስለሚሆን ገበሬዎች ከእጅ ወደ አፍ በሆነ የኑሮ ሁኔታ እንዲኖሩ ይገደዳሉ፡፡ የመሬቱ ምርታማነት ቢጨምር እንኳን በፍጥነት በማደግ ላይ ያለውን የሕዝብ ቁጥር መመገብ አይችልም፡፡ ይህ ሁኔታ ሰዎች ከገጠር ወደ ከተማ እንዲፈልሱ ያደርጋል፡፡ ከተሞች ደግሞ ያልታሰበ የሕዝብ ቁጥር ጫና ያጋጥማቸዋል፡፡

ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት የሥራ ዕድልን በከፍተኛ ሁኔታ ይቀንሳል፣ የመኖሪያ ቤት እጥረትን ያባብሳል፣ የትምህርት ዕድል ያሳጣል እንዲሁም የሕክምናንና የምግብ አቅርቦትን በከፍተኛ ሁኔታ ይቀንሳል፡፡ በተጨማሪም ማኅበራዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊና ፓለቲካዊ ቀውሶችን ያስከትላል፡፡ **ለምሳሌ፡-** ልመና፣ ስርቆት፣ ንጥቂያና የመሳሳሉት ማኅበራዊ ቀውሶች ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡ በከተሞች የምግብ አቅርቦት እጥረት ስለሚኖር የዋጋ ንረት ይከሰታል፡፡

ኢትዮጵያ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ከሚታይባቸው ሀገሮች በመጀመሪያው ረድፍ ላይ ትገኛለች፡፡ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ባላቸው ሀገሮች ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዙት ሕጻናት ናቸው፡፡ ስለዚህ ሕጻናትን ለመመገብ አነስተኛ ቁጥር ያለው አምራች የኅብረተሰብ ክፍል ብዙ መሥራት ይጠበቅበታል፡፡ በሥራ ላይ የሚሠማራው የሕዝብ ቁጥር አነስተኛ በሆነ ቁጥር የአንድ ሀገር የምጣኔ ሀብት ዕድገት ይቀጭጫል፡፡

ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት የሚያስከተለውን ተጽእኖ ለመቀነስ የቤተሰብ ዕቅድን መተግበር፣ ልጆችን በገቢ መጠን መጥኖና አራርቆ መውለድ ያስፈልጋል፡፡

## መልመጃ 3.7

**ሀ. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች አንብባችሁ ትክክል ከሆኑ "እውነት" ወይንም ትክክል ካልሆኑ ሐሰት በማለት መልሱ፡፡**

1. ሀገር የመልክዓ ምድር መጠሪያ ስያሜ ነው፡፡
2. ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪካ የምትገኝ ሉአላዊ ሀገር ናት፡፡
3. የጅቡቲ ሪፑብሊክ ኢትዮጵያን በስተምዕራብ ታዋስናለች፡፡
4. የሀገሮች መልካም ግንኙነት በምጣኔ ሀብታዊና በዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶች ይታወቃል፡፡
5. በኢትዮጵያ ከፍተኛው ተራራ የሚገኘው በሰሜን ምዕራብ ከፍተኛ ቦታዎች ነው፡፡

**ለ. በ"ለ"ሥር የተዘረዘሩትን በ"ሀ" ሥር ከተዘረዘሩት ውሃማ አካላት ጋር አዛምዱ፡፡**

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| ________1. በስፋት ስምጥ ሸለቆን ይሸፍናል | ሀ. ጣና |
| ________2. ወደ ደቡብ ይፈሳል | ለ. ዝዋይ |
| ________3. ከሰሜን ምዕራብ ይመነጫል | ሐ. ዋቢ ሸበሌ |
| ________4. ትልቁ ሐይቅ | መ. አዋሽ |
| ________5. ጥልቁ ሐይቅ | ሠ. ዓባይ |
| | ረ. አቢያታ |
| | ሰ. ሻላ |
| | ሸ. ጊቤ |
| | ቀ. ጫሞ |
| | በ. አሸንጌ |

**ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ መርጣችሁ መልሱ፡፡**

1. ከሚከተሉት አንዱ ከሰሜን ምዕራብ ከፍተኛ ቦታዎች ይነሣል፡፡
   ሀ. ገናሌ ለ. ዋቢ ሸበሌ ሐ. ዓባይ መ. ጁባ
2. ከሚከተሉት ውስጥ የስምጥ ሸለቆ ሐይቅ የሆነው የትኛው ነው?
   ሀ. ጣና ለ. ወንጪ ሐ. አሸንጌ መ. ሻላ
3. ከሚከተሉት አንዱ ብርቅዬ የኢትዮጵያ የዱር እንስሳ ነው፡፡
   ሀ. ቀጭኔ ለ. ዋልያ ሐ. ዝንጀሮ መ. ጅብ
4. በኢትዮጵያ በሕዝብ ቁጥር ብዛት ቀዳሚውን ሥፍራ የያዘው የትኛው ክልል ነው?
   ሀ. ጋምቤላ ለ. አማራ ሐ. ደቡብ መ. ኦሮሚያ
5. ከሚከተሉት አነስተኛ የሕዝብ ጥግግት ያለው የትኛው ዞን ነው
   ሀ. አኙዋክ ለ. ወላይታ ሐ. ጅማ መ. ጌዲኦ

መ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ

1. ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በመሬት አጠቃቀም ላይ የሚያስከትለው ችግር ምንድን ነው?
2. ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በውሃ አቅርቦት ላይ የሚያስከትለው ተጽእኖ ምንድን ነው?
3. ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በትምህርት ላይ የሚኖረው ጫና ምንድን ነው?
4. ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በጤና አጠባበቅና በመጠለያ ላይ ያለውን አሉታዊ ተጽእኖ ግለጹ፡፡

## 3.2. ዋና ዋና የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴዎች በኢትዮጵያ

**ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት**

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ግብርናን ሰብል ማምረት፣ የእንስሳት እርባታና ቅይጥ ግብርና በማለት ትመድባላችሁ፡፡
- ለሰብል ማምረትና ለከብት እርባታ ሥራ የሚረዱ የታወቁ መሣሪያዎችን ስሞች ትጠቅሳላችሁ፡፡
- ለሰብል ማምረትና ከብት እርባታ ሥራ የሚውሉ የታወቁ መሣሪያዎችን ትጠቀማላችሁ፡፡
- የኢንዱስትሪን ጠቀሜታ ታስረዳላችሁ፡፡
- ኢንዱስትሪዎችን የጎጆ ኢንዱስትሪ፣ ቀላል ኢንዱስትሪና ከባድ ኢንዱስትሪ በማለት ትመድባላችሁ፡፡
- በኢትዮጵያ የሚገኙ ዋና ዋና የኢንዱስትሪ አካባቢዎችን ስሞች ትጠቅሳላችሁ፡፡
- በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኙ ዋና ዋና ኢንዱስትሪዎች ምሳሌዎች ትሰጣላችሁ፡፡
- የቱሪዝምን ጠቀሜታ ታስረዳላችሁ፡፡
- ታዋቂ የጉብኝት ቦታዎችን መገኛ ትዘረዝራላችሁ፡፡
- የንግድን ጠቀሜታ ታስረዳላችሁ፡፡
- ንግድን የሀገር ውስጥና የውጭ ንግድ በማለት ትመድባላችሁ፡፡
- የሀገር ውስጥና የውጭ ንግድ ምሳሌዎችን ትሰጣላችሁ፡፡
- መጓጓዣ በኢትዮጵያ ዕድገት ውስጥ የሚጫወተውን ሚና ትገልጻላችሁ፡፡
- የቴክኖሎጂን ጠቀሜታ ታስረዳላችሁ፡፡
- ቴክኖሎጂ በግብርና፣ በኢንዱስትሪ፣ በመረጃና መገናኛ ዘርፍ እንዴት ተግባራዊ እንደሚሆን ታስረዳላችሁ፡፡
- የሸራብንና የጥልፍን ሥራ ትለማመዳላችሁ፡፡

**የንዑስ ርዕስ ይዘቶች**

1. ግብርና
2. ኢንዱስትሪ
3. ቱሪዝም
4. ንግድና መጓጓዣ
5. ቴክኖሎጂ ለዕድገት

## 1. ግብርና

ሰዎች ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት ከሚያደርጓቸው ውጤታማ እንቅስቃሴዎች አንዱ ግብርና ነው፡፡

**ተግባር 3.2.1** ☛ የቡድን ውይይት

**ዓላማ፡-** የግብርናን ምንነት መግለጽ

**መመሪያ፡-** ከ 3-5 በሚደርሱ አባላት ቡድን መሥርታችሁ ተወያዩ፡፡

**የመወያያ ጥያቄዎች**

- ግብርና ምንድን ነው?
- ሰዎች ለምን ከብት ያረባሉ?
- ወተትና ሥጋ የምን ውጤቶች ናቸው?

ግብርና ሰብል ማምረትንና ከብት ማርባትን ወይንም ሁለቱንም ማለትም ሰብል ማምረትንና ከብት ማርባትን ቀይጦ ማካሄድን የሚያጠቃልል ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ነው፡፡ በተጨማሪም የዶሮ እርባታ፣ የንብ እርባታና የመሳሰሉትን ያካትታል፡፡

### ሀ. የግብርና ዓይነቶች

ግብርና በተለያዩ የአየር ንብረት አካባቢዎች ይካሄዳል፡፡ ግብርና ልዩ ልዩ ግብአቶች ይፈልጋል፡፡

ግብአት ግብርናን ለማካሄድ የሚጠቅም ተፈጥሮአዊና ሰው ሠራሽ ነገር ነው፡፡

በጥቅሉ የግብርና ዓይነቶች በሦስት ይከፈላሉ፡፡ እነርሱም፡-

- የሰብል ምርት
- የከብት እርባታና
- ቅይጥ ግብርና ናቸው፡፡

**ተግባር 3.2.2** ☛ የቡድን ውይይት

**ዓላማ፡-** የግብርና ዓይነቶችን ልዩነትና አንድነት መግለጽ

**መመሪያ፡-** ከ 3-5 በሚደርሱ አባላት ቡድን መሥርታችሁ ተወያዩ፡፡

**የመወያያ ጥያቄዎች**

- የሰብል ምርት ምንድን ነው?
- የሰብል ምርት ከከብት እርባታ በምን ይለያል?
- ቅይጥ ግብርና ምንድን ነው?

## የሰብል ምርት

የሰብል ምርት የምግብ እህል፣ ጥራጥሬና የቅባት እህሎች ማምረትን ያጠቃልላል።

### የምግብ እህል

በኢትዮጵያ ልዩ ልዩ የምግብ እህሎች ይመረታሉ። እነርሱም ስንዴ፣ ገብስ፣ ጤፍ፣ በቆሎ፣ ዘንጋዳና ማሽላ ናቸው። በአጠቃላይ ስንዴ፣ ገብስና ጤፍ በኢትዮጵያ ከፍተኛ ቦታዎች ይበቅላሉ።



ስንዴ



ጤፍ



ገብስ

ሥዕል 3.7 በከፍተኛ ቦታዎች የሚበቅሉ የምግብ እህሎች

በቆሎ፣ ዘንጋዳና ማሽላ በዝቅተኛ ቦታዎች ይበቅላሉ።



ዘንጋዳ



በቆሎ




ማሽላ

ሥዕል 3.8 በዝቅተኛ ቦታዎች የሚበቅሉ የምግብ እህሎች

### ጥራጥሬ

አተር፣ ሽንብራ፣ ምስርና ባቄላ ጥራጥሬ ተብለው ይታወቃሉ። ጥራጥሬዎች በስፋት የሚመረቱት በከፍተኛ ቦታዎች ነው።



ምስር

ሥዕል 3.9 በከፍተኛ ቦታዎች የሚበቅል ጥራጥሬ

### የቅባት እህሎች

በኢትዮጵያ የተለያዩ የቅባት እህሎች ይበቅላሉ። በጣም የታወቁት የቅባት እህሎች ተልባ፣ ኑግ፣ ሰሊጥ፣ ሱፍና ለውዝ ናቸው። የቅባት እህሎች ተስማሚ ሙቀት ባለው አካባቢ ይበቅላሉ። ሰሊጥ ለውጭ ንግድ ከሚላኩ የቅባት እህሎች ቀዳሚውን ሥፍራ ይይዛል።


ተልባ


ሰሊጥ


ለውዝ

ሥዕል 3.10 የቅባት እህሎች

### እንሰት

እንሰት ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ባላቸው አካባቢዎች በተለይም ከፍተኛ የሕዝብ ጥግግት ባላቸው በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልል በሚገኙ አካባቢዎች ይበቅላል፡፡ እንሰት በይበልጥ በጉራጌ ዞን፣ በከምባታና ጥምባሮ፣ በወላይታ፣ በጋሞ ጎፋና በመሳሰሉት አካባቢዎች ተወዳጅ ምግብ ነው፡፡


ሥዕል 3.11 እንሰት

**ተግባር 3.2.3** ☛ የቡድን ሥራ

**ዓላማ፡-** የተለያዩ የሰብል ዓይነቶችን ናሙና መሰብሰብና ለእይታ ማብቃት

**መመሪያ፡-** ከ3-5 በሚደርሱ አባላት ቡድን መሥርታችሁ የሰብል ዓይነቶችን ናሙና ሰብስቡ ፡፡

**ናሙና የሚሰበሰብባቸው የሰብል ዓይነቶች**

- እህል፡- ስንዴ፣ ገብስ፣ ጤፍ፣ በቆሎ፣ ዘንጋዳ፣ ማሽላ
- ጥራጥሬ፡- አተር፣ ሽንብራ፣ ምስር፣ ባቄላ
- የቅባት እህሎች፡- ተልባ፣ ኑግ፣ ሰሊጥ፣ ለውዝ፣ ሱፍ

**አስፈላጊ መሣሪያ፡-**

- ላስቲክ፣ ማሸጊያ ላስቲክ፣ ሻማ፣ ክብሪት
- ናሙናውን መለጠፊያ ካርቶን፡፡


**የአተገባበር ቀደም ተከተል**

- ለእያንዳንዱ የሰብል ዓይነት የላስቲክ ከረጢት በመሥራት እህሉን በመጨመር ማሸግ፡፡
- የናሙናውን ስም ወረቀት ላይ ጽፎ ከረጢቱ ላይ መለጠፍ፡፡
- ናሙናውን ለእይታ በሚያመች ቦታ ማስቀመጥ፡፡

## ከብት እርባታ

ኢትዮጵያ በርካታ የቀንድና የጋማ ከብት አላት፡፡ ፍየል፣ በግ፣ በሬና ላም የቀንድ ከብቶች ይባላሉ፡፡ ግመል፣ አህያ፣ ፈረስና በቅሎ የጋማ ከብት በመባል ይታወቃሉ፡፡ እነዚህ እንስሳት በሀገሪቱ ከፍተኛና ዝቅተኛ ቦታዎች ይገኛሉ፡፡

በጣም ቆላማና በረሃማ በሆኑ አካባቢዎች ግመሎችና ፍየሎች በብዛት ይራባሉ፡፡ በአብዛኛው ግመሎችና ፍየሎች የሚራቡት በሰሜን ምሥራቅና በደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ ነው፡፡ ኑሮአቸውን በከብት እርባታ ላይ ያደረጉ ገበሬዎች አርብቶ አደር ይባላሉ፡፡ አርብቶ አደር የተባሉበት ምክንያት ሕይወታቸው በከብት እርባታ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ነው፡፡ አርብቶ አደሮች ከግመልና ፍየል በተጨማሪ የቀንድ ከብቶችም ያረባሉ፡፡

ሥዕል 3.12 የቆላማና በረሃማ አካባቢዎች እንስሳት

## ቅይጥ ግብርና

ቅይጥ ግብርና ከሰብል ማምረቱ ሥራ በተጓዳኝ እንስሳት እያረቡ የሚኖሩበት የግብርና ዓይነት ነው፡፡

በቅይጥ የግብርና ዘርፍ ገበሬዎች የተለያዩ ሰብሎችን ያመርታሉ፡፡ በተጨማሪም ልዩ ልዩ የቤት እንስሳትን ያረባሉ፡፡ ይህ ዓይነቱ የግብርና እንቅስቃሴ በሰሜን ምዕራብና በደቡብ ምሥራቅ ከፍተኛ ቦታዎች ላይ በብዛት የተለመደ ነው፡፡ በኢትዮጵያ 80 በመቶ የሚደርሱ ገበሬዎች ኑሮ የተመሠረተው በቅይጥ ግብርና ላይ ነው፡፡ ነገር ግን በከፍተኛ ቦታዎች የሚገኙ ገበሬዎች ከከብት እርባታ ይልቅ ለሰብል ምርት ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣሉ፡፡

**ተግባር 3.2.4** ☛ **የቡድን ውይይት**

**ዓላማ፡-** የከብት እርባታንና የቅይጥ ግብርናን ልዩነትና አንድነት መግለጽ

**መመሪያ፡-** ከ 3-5 በሚደርሱ አባላት ቡድን መሥርታችሁ ተወያዩ፡፡

**የመወያያ ጥያቄዎች**

- ከብት እርባታ ከቅይጥ ግብርና በምን ይለያል?
- ከብት እርባታንና ቅይጥ ግብርናን የሚያመሳስላቸው ምንድን ነው?
- ከብት እርባታ ለምን በዝቅተኛ ቦታዎች ይካሄዳል?
- በከፍተኛ ቦታዎች የሚገኙ ገበሬዎች ለምን ቅይጥ ግብርናን ይጠቀማሉ?

ሰብል ለማምረትና ለከብት እርባታ የሚውሉ የታወቁ መሣሪያዎች

የሰብል ምርት ለማምረት ልዩ ልዩ መሣሪያዎች ያስፈልጋሉ:: መሣሪያዎቹ ባህላዊ ወይንም ዘመናዊ ሊሆኑ ይችላሉ:: ባህላዊ መሣሪያዎች ምርታማነታቸው አነስተኛ ነው:: ዘመናዊ መሣሪያዎች ምርታማነታቸው ከፍተኛ ነው:: መኮትኮቻ፣ አካፋ፣ መቧጠጫ፣ መንሽ፣ ማረሻ፣ መከስከሻ፣ ሞፈር፣ ቀንበር፣ እርፍ፣ መጥረቢያ፣ ማጭድና፣ ገጀራ ባህላዊ የማምረቻ መሣሪያዎች ናቸው:: ዘመናዊ የሰብል ማምረቻ መሣሪያዎች ትራክተርን፣ መከስከሻን፣ ማጨጃና መውቂያ ማሽኖችን ያካትታሉ::

## ለከብት እርባታ የሚጠቅሙ መሣሪያዎች

ከብት እርባታን ውጤታማ ለማድረግ የተለያዩ ባህላዊና ዘመናዊ መሣሪያዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ:: ከብት እርባታ ለሁለት ዓላማዎች ሊካሄድ ይችላል:: አንደኛው ለወተት ምርት ሲሆን ሁለተኛው የሥጋ ምርት ለማግኘት ነው:: ዘመናዊ መሣሪያዎች ጥራት ያላቸውና ምርታማ እንስሳትን ለማርባት ይጠቅማሉ:: በተጨማሪም የእንስሳቱ ጤንነት እንዲጠበቅ ምርታቸውም ጤናማና አስተማማኝ እንዲሆን ያግዛሉ:: የከብቶች መመገቢያ ቤት፣ ውኃ መጠጫ ገንዳ፣ ወተት የሚታለብበት ቀላል ማሽን፣ የአካባቢውን ንጽሕና መጠበቂያ መሣሪያዎች በዘመናዊ የማምረቻ መሣሪያዎች ሥር ይጠቃለላሉ::



ሥዕል 3.13 ዘመናዊ የከብት እርባታ

**ተግባር 3.2.5** ☛ **የቡድን ሥራ**

**ዓላማ:-** ሰብሎችን ማብቀልና መንከባከብ

**መመሪያ:-** ከ 3-5 አባላት ያሉት ቡድን መሥርታችሁ ሰብሎችን አብቅሉና ተንከባከቡ

**የክንውን ተግባራት**

- የእህል ዘር ወይንም ጥራጥሬ ማብቀያ ሥፍራ አዘጋጁ::
- የእህሉን ዘር ወይንም ጥራጥሬውን በመሥመር ዝሩ::
- በየቀኑ ጧትና ከ10 ሰዓት በኋላ ውሃ አጠጡት::
- ችግኙን በየጊዜው እያረማችሁ ኮትኩቱት::
- ያፈራው ምርት እንዳይበላሽ ጠብቁ::
- ምርቱ መድረሱ ሲረጋገጥ ሰብስቡት::

## መልመጃ 3.8

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ**

1. ግብርና ምንድነው?
2. ግብርና በስንት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል?
3. የሰብል ምርት ምን ምንን ያጠቃልላል?
4. የምግብ እህል ከጥራጥሬና ከቅባት እህሎች በምን ይለያል?
5. የእንስሳት እርባታ ከሰብል ምርት በምን ይለያል?
6. በኢትዮጵያ የከብት እርባታ የሚካሄደው በየት አካባቢ ነው?
7. ቅይጥ ግብርና ምንድነው?
8. ቅይጥ ግብርና በኢትዮጵያ የሚካሄድባቸውን አካባቢዎች ዘርዝሩ::
9. ለሰብል ምርትና ለከብት እርባታ የሚያስፈልጉ መሣሪያዎችንና ጠቀሜታቸውን አስረዱ::

## 2. ኢንዱስትሪ

ኢንዱስትሪ በግብርና የተገኙ ጥሬ ዕቃዎችን ወይንም ሌሎች በተፈጥሮ የተገኙ ሀብቶችን በመጠቀም ወደ ሌላ የምርት ዓይነት የመለወጥ አገልግሎት የሚስጥበት ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ነው:: ይህ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ የግብርና ውጤቶችን ወይንም የተፈጥሮ ሀብትን በከፊል ወይንም ሙሉ በሙሉ የመለወጥ ሂደትን ያካትታል::

**ኢንዱስትሪዎች በሦስት ይከፈላሉ:: እነርሱም:-**

ሀ. የጎጆ ኢንዱስትሪዎች


ለ. ቀላል ኢንዱስትሪዎች

ሐ. ከባድ ኢንዱስትሪዎች ናቸው::

### ሀ. የጎጆ ኢንዱስትሪዎች

በሰው ልጅ የዕድገት ታሪክ ውስጥ ቀዳሚውን ሥፍራ የሚይዙት የጎጆ ኢንዱስትሪዎች ናቸው:: የጎጆ ኢንዱስትሪዎች ቀላል መሣሪያዎችን በመጠቀም ኅብረተሰብ ሊጠቀምባቸው የሚችሉ አልባሳትና ልዩ ልዩ ቁሳቁስ ያመርታሉ:: የጎጆ ኢንዱስትሪዎች ልብስን፣ የብረታ ብረት ሥራን፣ የእንጨት ሥራን፣ የቆዳ ሥራን ፣ የሸክላ ሥራንና የመሳሰሉትን ያጠቃልላሉ::

የጎጆ ኢንዱስትሪዎች በገጠርም ሆነ በከተሞች አካባቢ በብዛት ይታያሉ:: ለዚህ ዋናው ምክንያት በትንሽ ቦታና የገንዘብ አቅም ሊቋቋሙ መቻላቸው ነው::



ሥዕል 3.14 የጎጆ ኢንዱስትሪዎች

### ለ. ቀላል ኢንዱስትሪዎች

ቀላል ኢንዱስትሪዎች በአብዛኛው ለውጭ ገበያ የሚውሉ ምርቶችን የሚያመርቱ ተቋማት ናቸው:: ቀላል ኢንዱስትሪዎች ጥሬ ዕቃዎቻቸውን ከግብርና እንዲሁም በከፊል ከተዘጋጁ የደንና የማዕድን ሀብቶች ያገኛሉ::

**ቀላል ኢንዱስትሪዎች:-**

- የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች
- ምግብ ማቀናበሪያ ፋብሪካዎች
- የወረቀት ፋብሪካ
- የሕትመት ፋብሪካ
- የቆዳ ውጤት ፋብሪካ
- የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎችንና መገጣጠሚያዎችን ያጠቃልላሉ::

በኢትዮጵያ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች በኮምቦልቻ፣ በድሬደዋ፣ በአዲስ አበባ፣ በባሕርዳር፣ በሐዋሳና በትግራይ ይገኛሉ:: ምግብ ማቀናበሪያ ፋብሪካዎች ደግሞ በብዛት በአዲስ አበባ፣ በአዳማና በድሬዳዋ ከተሞች ይገኛሉ:: ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ ንግድ ማተሚያ

ድርጅት፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅትና የመሳሰሉት በአዲስ አበባ የሚገኙ የሕትመት ፋብሪካዎች ናቸው፡፡

## ሐ. ከባድ ኢንዱስትሪዎች

ከባድ ኢንዱስትሪዎች በሰፊ ሥፍራ ላይ የሚቋቋሙ ናቸው፡፡ ምርት ለማምረት ትላልቅና ውስብስብ ሥራ የሚያከናውኑ ከባድ የማምረቻ መሣሪያዎችን ይጠቀማሉ፡፡ የጥሬ ሀብት ግብአታቸውም በጣም ብዙ ሲሆን ለእንቅስቃሴያቸውም ከፍተኛ የገንዘብ አቅምና እጅግ የሰለጠነ የሰው ኃይል ይፈልጋሉ፡፡

### ከባድ ኢንዱስትሪዎች፡-

- የነዳጅ ማጣሪያዎችን
- የመኪናዎችና የአውሮፕላን ማምረቻዎችን
- የኬሚካል ማምረቻዎችን
- የሲሚንቶ ማምረቻዎችንና
- የባቡር ማምረቻዎችን ያጠቃልላሉ፡፡

**ለምሳሌ** በኢትዮጵያ የሲሚንቶ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ከአዲስ አበባ በተወሰነ ርቀት በሞጆ፣ በደርባና፣ በሙገር እንዲሁም በድሬዳዋና በመቀሌ ከተሞች ይገኛሉ፡፡

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ዋና ዋና የኢንዱስትሪ አካባቢዎች በመባል የሚታወቁት አዲስ አበባ፣ አዳማ፣ ባሕር ዳር፣ መቀሌና ሐዋሳ ናቸው፡፡



ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ



የነዳጅ ማጣሪያ

ሥዕል 3.15 ቀላል እና ከባድ ኢንዱስትሪ

**ተግባር 3.2.6** ☛ **የቡድን ሥራ**

**ዓላማ:-** የኢንዱስትሪ ዓይነቶችን ማነጻጸር

**መመሪያ:-** ከ 3 -5 በሚደርሱ አባላት ቡድን መሥርታችሁ ተወያዩ::

**የመወያያ ጥያቄዎች**

- የጎጆ ኢንዱስትሪ ከቀላል ኢንዱስትሪ የሚለየው በምንድን ነው?
- ቀላል ኢንዱስትሪ ከከባድ ኢንዱስትሪ በምን ይለያል?

## መልመጃ 3.9

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ**

1. ኢንዱስትሪ ምንድን ነው?
2. ከጎጆ ኢንዱስትሪ ምርቶች ሦስት ጥቀሱ::
3. በኢትዮጵያ ቀላል ኢንዱስትሪዎች የሚገኙባቸውን አካባቢዎች ዘርዝሩ::
4. በአብዛኛው ቀላል ኢንዱስትሪዎች የሚጠቀሙባቸውን ጥሬ ሀብቶች ከየት ያገኛሉ?
5. በኢትዮጵያ የሚገኙ የከባድ ኢንዱስትሪ ምሳሌዎችን ጥቀሱ::

### 3. ቱሪዝም

ቱሪዝም የሰዎች ለጉብኝት ከቦታ ወደ ቦታ መንቀሳቀስን ያመለክታል:: ሰዎች በራሳቸው አነሣሽነት አካባቢያቸውን ለቀው በቅርብ ወይም በሩቅ ርቀት አስደናቂና አስገራሚ ነገሮችን ለማየት የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ጉብኝት /tourism/ ይባላል::

ቱሪዝም ለአንድ ቡድን፣ ወገን ወይም ግለሰብ መዝናናትንና ደስታን የሚያጎናፅፍ እንቅስቃሴ ነው::

ቱሪዝም እንዲካሄድ ተፈጥሯዊ ወይም ሰው ሠራሽ መስህብ ያስፈልጋል:: የቱሪዝም መስህብ አካባቢዎች ሰዎችን ወደ ራሳቸው ይስባሉ:: ወደ አንድ አካባቢ በጉብኝት የሚመጡ ሰዎች ለአካባቢው ሕዝብ ገቢ ያስገኛሉ:: ገቢው በቀረጥ መልክ፣ በአገልግሎት ክፍያ፣ ባህላዊ ቁሳቁስ በመሸጥ፣ ታሪካዊና ቅሪተ አካላት የሚገኙበትን ቤተ መዘክር በማስጎብኘት ሊገኝ ይችላል:: ቱሪስቶች ወደ አንድ ሀገር በሕጋዊ መልክ ሲገቡ የውጭ ምንዛሪ ይዘው ስለሚመጡ ለተቀባይ ሀገር ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው:: ቱሪዝም ለአንድ አካባቢ ሕዝብ የሥራ ዕድል በመፍጠርም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል::

**ተግባር 3.1.2.7** ☛ የቡድን ሥራ

ዓላማ:- በቱሪዝም ጠቀሜታ ላይ መወያየት

መመሪያ:- ከ 3-5 በሚደርሱ አባላት ቡድን መሥርታችሁ ተወያዩ።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

- ቱሪዝም ምንድን ነው?
- የቱሪዝም ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታ ምንድን ነው?
- የጉብኝት መነሻዎች ምንድን ናቸው?

## ብሔራዊ ፓርኮችና ጥብቅ የተፈጥሮ አካባቢዎች

በኢትዮጵያ ውስጥ በርካታ የጎብኚ መስህቦች ይገኛሉ። የጎብኚ መስህቦች፣ ብሔራዊ ፓርኮችና ጥብቅ የተፈጥሮ አካባቢዎች በዙሪያቸው በሚገኙ ሕዝቦች ጥበቃና እንክብካቤ ይደረግላቸዋል። የአካባቢውም ሕዝብም ይህንን በማድረጉ ተጠቃሚ ይሆናል።

**ሰንጠረዥ 3.13 ብሔራዊ ፓርኮችና ጥብቅ የተፈጥሮ አካባቢዎች**

| ተ.ቁ | ብሔራዊ ፓርክ | መገኛ | ጥብቅ የተፈጥሮ አካባቢዎች | መገኛ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አቢያታና ሻላ ሐይቆች ብሔራዊ ፓርክ | ስምጥ ሸለቆ | ባቢሌ የዝሆን መከለያና መጠበቂያ | ከሐረር በስተደቡብ ምሥራቅ |
| 2 | አዋሽ ብሔራዊ ፓርክ | ላይኛው ስምጥ ሸለቆ | ቁኒ ሙክታር የኒያላ መከለያና መጠበቂያ | በድሬደዋ መስመር ከጪሮ በስተ ምዕራብ |
| 3 | የባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ | ባሌ ዞን | ሰንቀሌ የቆርኪ መከለያና መጠበቂያ | ከአዲስ አበባ በስተ ደቡብ (ሻሸመኔ-ሶዶ አውራ ጐዳና ላይ) |
| 4 | ጋምቤላ ብሔራዊ ፓርክ | ጋምቤላ | ያቤሎ መከለያና መጠበቂያ | ወደ ሞያሌ በሚያመራው አውራ ጎዳና (ኬንያና-ኢትዮጵያ ድንበር ላይ) |
| 5 | ማጎ ብሔራዊ ፓርክ | ጋሞጎፋ | - | - |
| 6 | ነጭ ሣር ብሔራዊ ፓርክ | አርባ ምንጭ አካባቢ | - | - |
| 7 | ኦሞ ብሔራዊ ፓርክ | በኦሞ ወንዝ ምዕራባዊ ዳርቻ | - | - |
| 8 | ስሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ | ሰሜን ጎንደር | - | - |
| 9 | ያንጉዲራሳ ብሔራዊ ፓርክ | አፋር | - | - |

ኢትዮጵያ ከተፈጥሮ አካባቢዎች በተጨማሪ የጎብኚዎች መስህብ የሆኑ ታሪካዊ ሥፍራዎች፣ ዋሻዎችና ትክል ድንጋዮች አሏት፡፡

### ሰንጠረዥ 3.14 ታሪካዊ ሥፍራዎችና መገኛቸው

| ተ.ቁ | ታሪካዊ ሥፍራ | መገኛ |
|---|---|---|
| 1 | የአክሱም ሐውልት | ትግራይ (አክሱም) |
| 2 | የጎንደር አብያተ መንግሥታት | አማራ (ጎንደር) |
| 3 | የላሊበላ አብያተ ክርስቲያን | አማራ (ላሊበላ) |
| 4 | የሐረር ግንብ | ሐረር |
| 5 | የጥያ ትክል ድንጋይ | ደቡብ ሕዝቦች (ጉራጌ ዞን) |
| 6 | የሶፍ ዑመር ዋሻ | ኦሮሚያ (ባሌ ዞን) |

## መልመጃ 3.10

የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ

1. ቱሪዝም ምንድን ነው?
2. የቱሪዝም ጠቀሜታ ምንድን ነው?
3. ለጎብኚዎች መስህብ ከሆኑት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ፓርኮችና ጥብቅ የተፈጥሮ አካባቢዎች ሦስት ሦስት ምሳሌዎች ስጡ፡፡
4. ለጎብኚዎች መስህብ ከሆኑት የኢትዮጵያ ታሪካዊ ሥፍራዎች አራት ምሳሌዎችን ስጡ፡፡

### 4.ንግድና መጓጓዣ

እቃን በእቃ ወይም ሰብልን በሰብል አለበለዚያም እቃን ወይም ሰብልን በገንዘብ የመለወጥ ሂደት ንግድ ይባላል፡፡

#### ሀ. የንግድ ጠቀሜታ

ንግድ አልባሳትን፣ ቁሳቁስን፣ የምግብ እህልን፣ እንስሳትንና በአጠቃላይ የተለያዩ ምርቶችን ከአምራቾች ወደ ተጠቃሚዎች ለማድረስ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ የግብርና ውጤቶችንም ሆነ የፋብሪካ ምርቶችን ወደ ተጠቃሚው ለማድረስ የንግድ ልውውጥ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

ንግድ ለምጣኔ ሀብት ዕድገት የሥራ ዕድል በመፍጠር ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ ንግድ ትርፍ ገንዘብ ስለሚያስገኝ ለመንግሥታት የልማት ሥራ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም ንግድ የባህል ልውውጥ እንዲፈጠር ምክንያት ይሆናል፡፡ ሰዎች ከመኖሪያ አካባቢያቸው ርቀው ሄደው በሚያደርጉት የሸቀጥ ግዥና ሽያጭ እንቅስቃሴ የባህል ልውውጥ ያደርጋሉ፡፡ በዚህም ምክንያት በአንድ አካባቢ የማይታወቁ አለባበሶች፣ የሰላምታ

አለዋወጥ፣ የአነጋገር፣ አመጋገብና ሌሎች ባህሎች ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላ አካባቢ ሊስፋፉ ይችላሉ፡፡

### ሰ. የሀገር ውስጥና የውጭ ንግድ

ንግድ የሀገር ውስጥና የውጭ ንግድ ተብሎ በሁለት ይከፈላል፡፡

### የሀገር ውስጥ ንግድ

ንግድ በአንድ በተወሰነ አካባቢ ወይም በሰፊ ሥፍራ ሊወሰን ይችላል፡፡ በአካባቢያችሁ የሚገኙ ሱቆች፣ የገበያ ማዕከላት፣ በየዕለቱ ወይም በየሳምንቱ የሚታዩ ገበያዎች የንግድ እንቅስቃሴ የሚካሄድባቸው ናቸው፡፡ የጅምላና የችርቻሮ የንግድ ልውውጥ እንቅስቃሴዎችም የንግድ አካላት ናቸው፡፡

ሸቀጦች ወይም የግብርና ውጤቶች በተመረቱበት አካባቢ ወይም ከአካባቢያቸው ራቅ ብለው የሚዘዋወሩበት የልውውጥ እንቅስቃሴ የሀገር ውስጥ ንግድ ይባላል፡፡ የሀገር ውስጥ ንግድ በአንድ ሀገር ሉአላዊ ወሰን ውስጥ የሚካሄድ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ነው፡፡ ንግድ በሁለት ወይም በሦስት ወገኖች መካከል የሚካሄድ በስምምነትና በጠቀሜታ ላይ የተመሠረተ የልውውጥ ሂደት ነው፡፡ የንግድ ሸቀጥ አቅራቢዎች ነጋዴዎች ሲሆኑ ከፍላጎታቸው አንጻር ሸቀጡን ገዝተው የሚጠቀሙት ደግሞ ደንበኞች ወይንም ሸማቾች ናቸው፡፡ በነጋዴዎችና በሸማቾች መካከል ለሚፈጠረው ግንኙነት ስምምነት እንዲኖር የሚያደርጉ ሰዎች አሉ፡፡ እነዚህ ለስምምነቱ ፊር መያዝ ጊዜና ችሎታቸውን ተጠቅመው ነጋዴዎችና ሸማቾችን ወይንም ገዢና ሻጭን የሚያገናኙ ሰዎች አዋዋዮች ወይም ደላሎች ይባላሉ፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ በከተሞችና በክልሎች መካከል የሚካሄደው የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶች ልውውጥ የሀገር ውስጥ ንግድ ይባላል፡፡

### የውጭ ንግድ

ሀገሮች በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚኖሯቸው ስምምነቶች አንዱ ንግድ ነው፡፡ ንግዱ የሚካሄደው በሁለት ወይም ከሁለት በላይ በሆኑ ሀገሮች መካከል ሊሆን ይችላል፡፡ የንግድ ልውውጡ ጥራቱን በጠበቀ የግብርና ወይም የፋብሪካ ውጤት አለበለዚያም በሁለቱም የምጣኔ ሀብት ዘርፍ ምርቶች ላይ የተመሠረተ ይሆናል፡፡ ሀገሮች ጥራታቸውን የጠበቁ ምርቶችና ሸቀጣሸቀጦች ይዘው በዓለም ገበያ ላይ ሲቀርቡ ተቀባይነታቸው ከፍ ስለሚል የገቢ ምንጫቸው ይጎለብታል፡፡ በዓለም ገበያ ላይ ጥራት ያለው የግብርናና የፋብሪካ ወይም የግብርና ወይም የፋብሪካ ምርት በማቅረብ የመስጠትና የመቀበል ልውውጥ የሚደረግበት ምጣኔ ሀብታዊ ሥርዓት የውጭ ንግድ ይባላል፡፡

ኢትዮጵያ ትልልቅ ፋብሪካዎችን ለማቋቋም የማምረቻ መሣሪያዎችን ከውጭ ገዝታ ታስገባለች፡፡ ብረታ ብረት፣ መኪናዎች፣ አውሮፕላኖች፣ የምግብ ሸቀጣ ሸቀጦች፣

መድኃኒትና ነዳጅ ከውጭ ከምታስገባቸው ሸቀጣ ሸቀጦች ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ ኢትዮጵያ ቡና፣ ቆዳና ሌጦ፣ የቅባት እህሎችና የአበባ ምርት ለውጭ ገበያ ታቀርባለች፡፡

**ተግባር 3.2.8** ☛ **የቡድን ውይይት**

**ዓላማ፡-** በንግድ ጠቀሜታና በንግድ ዓይነቶች ላይ ማብራሪያ መስጠት

**መመሪያ፡-** ከ 3 - 5 በሚደርሱ አባላት ቡድን መሥርታችሁ ተወያዩ፡፡

**የመወያያ ጥያቄዎች**

- ንግድ ምንድን ነው?
- ንግድ እንዲኖር ምን ምን ያስፈልጋል?
- የንግድ ጠቀሜታ ምንድን ነው?
- የሀገር ውስጥና የውጭ ንግድ ልዩነትና አንድነት ምንድን ነው?
- ኢትዮጵያ በውጭ ንግድ አማካኝነት ከምታስገባቸው ሸቀጦች ጥቂቱን ጥቀሱ፡፡

### መጓጓዣ

መጓጓዣ ሰዎችንና ምርትን ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላ አካባቢ ለማንቀሳቀስ የሚያስችል የግንኙነት መረብ ነው፡፡ መጓጓዣን ውጤታማ ለማድረግ የመኪና መንገድ፣ የባቡር መስመር፣ የአውሮፕላን አገልግሎትና የመርከብ አገልግሎት ያስፈልጋል፡፡ በባህላዊ ዘዴም የጋማ ከብቶች በመጓጓዣነት ሥራ ላይ ይውላሉ፡፡ በኢትዮጵያ በከተሞችና በክልሎች መካከል የሚካሄደው ንግድ ውጤታማ የሚሆነው በመጓጓዣ አማካኝነት ነው፡፡ መጓጓዣ ለሀገር ዕድገት በጣም አስፈላጊና ወሳኝ ነው፡፡

የሀገር ውስጥና የውጭ ንግድ ውጤታማ የሚሆኑት በመጓጓዣ አማካይነት ነው፡፡ ለሀገር ውስጥ ንግድ ትላልቅ መኪናዎች፣ አውሮፕላኖችና ባቡሮች ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡ ለውጭ ንግድ ደግሞ አውሮፕላንና መርከብ ሥራ ላይ ይውላሉ፡፡ አዋሳኝ ድንበር ባላቸው ሀገሮች መካከል ትላልቅ መኪናዎችና ባቡር የመጓጓዣ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡



የጭነት መኪና



ባቡር



አውሮፕላን

ሥዕል 3.16 ልዩ ልዩ ዘመናዊ መጓጓዣዎች

### የመጓጓዣ ሚና ለዕድገት

መጓጓዣ የምጣኔ ሀብት የደም ሥር ነው፡፡ በግብርናው ዘርፍ የተመረቱት ምርቶች ወደ ገበያ እንዲመጡ አውራ ጎዳናና ማጓጓዣ መኪና ያስፈልጋል፡፡ በኢትዮትጵያ ከግብርናው ዘርፍም ሆነ ከኢንዱስትሪው የሚገኙ ምርቶች ወደ ውጭ ገበያ ለመድረስ መጓጓዣ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ከውጭ ገበያ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ መሣሪያዎች፣ ብረታ ብረት፣ ኬሚካሎች፣ አልባሳት፣ የምግብ ሸቀጣ ሸቀጦች፣ መድኃኒቶች፣ የጥናትና ምርምር መሣሪያዎች፣ የትምህርት መጻሕፍትና መሣሪያዎች የሚጓጓዙት በመኪና መንገድ፣ በባቡር መስመር፣ በአውሮፕላንና በመርከብ ነው፡፡ እነዚህ ቁሳቁስና መሣሪያዎች ሀገር ውስጥ በመድረሳቸው በሁሉም የእንቅስቃሴ ዘርፍ ያሉት ተግባራት ተሟልተው ይካሄዳሉ፡፡ እነዚህ ተግባራት በተሟሉ መጠን ለሀገሪቱ ምጣኔ ሀብት ዕድገትና ለቴክኖሎጂ ለውጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡

## መልመጃ 3.11

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ**

1. የሀገር ውስጥ ንግድ ጠቀሜታን አስረዱ፡፡
2. የውጭ ንግድ ጠቀሜታን ግለጹ፡፡
3. በአካባቢያችሁ የሚታዩትን የንግድ እንቅስቃሴዎች ግለጹ፡፡
4. የንግድና የመጓጓዣን ትስሥር አብራሩ፡፡
5. መጓጓዣ ለኢትዮጵያ ምጣኔ ሀብታዊ እድገት የሚኖረውን አስተዋጽኦ ግለጹ፡፡

## 4. ቴክኖሎጂ ለዕድገት

### ሀ. የቴክኖሎጂ ትርጉም

ቴክኖሎጂ ማለት ዕድገት ለማምጣት አዳዲስ ነገሮችን በመፍጠር ሥራ ላይ ማዋል ማለት ነው፡፡ በሥራ ላይ የነበሩ መሣሪያዎችን፣ ማሽኖችን፣ የአሠራር ስልትን ማሻሻልና ያለቀ ግብ ላይ መድረስ ማለትም ይሆናል፡፡

### ለ. የቴክኖሎጂ ጥቅም

ቴክኖሎጂ በተለያዩ የምጣኔ ሀብት ዘርፎች ላይ ለውጥ ያመጣል፡፡ የቴክኖሎጂ ዕድገት መሣሪያዎችን በማሻሻል የዕውቀትና የአመራረት ስልት መሻሻል ያስከትላል፡፡ ሰዎች አንድን ነገር ወደ ሌላ ለማጓጓዝ በራሳቸውና በእንስሳት ጉልበት ይጠቀሙ ነበር፡፡ ነገር ግን ይህንን ችግር ለመፍታት ባደረጉት ጥረት መኪና ተፈጥሯል፡፡ መኪና በመፈጠሩ በአጭር ጊዜና በፍጥነት ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላው አካባቢ ቁሳቁሶችን ማጓጓዝ ተችሏል፡፡

በግብርናው ዘርፍ በሬዎችን ጠምዶ ወይም በፈረስ አማካኝነት ሲከናወን የነበረው ባህላዊ የአስተራረስ ዘዴን ለመለወጥ በተደረገው ጥረት ትራክተሮች ተፈጥረዋል፡፡ ምርትን ወቅቶ ለመሰብሰብ የሚያስችል ከምባይን ሃርቨስተር ተፈልስፏል፡፡ ይህም የግብርናው ምርታማነት በእጥፍ እንዲጨምር አስችሏል፡፡ ከብት እርባታን በዘመናዊ መልክ መምራት የተቻለው ቴክኖሎጂ ባስከተለው ለውጥ ነው፡፡ ወተት በማሽን ማለብ፣ ወተት ማጣራት፣ ቅቤ ማምረት መቻልና ንጹሕ ወተት ማቅረብ የተቻለው ቴክኖሎጂ ባመጣው ለውጥ ነው፡፡

### ሐ. የቴክኖሎጂ አተገባበር

ባለንበት ዘመን የመረጃ ልውውጥ በጣም ፈጣን ነው፡፡ በዚህ ምክንያት በግብርናው፣ በኢንዱስትሪው፣ በመጓጓዣ፣ በንግድ ልውውጥ፣ በትምህርት፣ በጤናና በመሳሰሉት ዘርፎች ዕድገት ላይ ቴክኖሎጂ ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡

በግብርናው ዘርፍ የነበሩ ባህላዊ የአስተራረስ ዘዴዎች በአዲስ የአስተራረስ ዘዴዎች መተካት፣ አዳዲስ መሣሪያዎች፣ የተሻሻሉ ምርጥ ዘሮች፣ የአረም ማጥፊያዎችና የመሳሰሉት ግኝቶች የቴክኖሎጂ ውጤቶች ናቸው፡፡

ቴክኖሎጂ በኢንዱስትሪ ዘርፍ አዳዲስ መሣሪያዎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሠራተኞች ደኅንነት እንዲጠበቅና የምርት መጠንና ጥራት እንዲጨምር አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ ይህም የገቢ መጠን ከፍ እንዲልና የኢንዱስትሪ ማስፋፋት ሥራ እየተጠናከረ እንዲሄድ ያስችላል፡፡ ስለዚህም ቴክኖሎጂ በሀገር ምጣኔ ሀብት ዕድገት ላይ አወንታዊ ለውጥ ይፈጥራል፡፡ ይህ ለውጥ ደግሞ በማኅበራዊ አገልግሎቶች ዕድገት ላይ ግልጽ መሻሻል ያስከትላል፡፡

ቴክኖሎጂ በመረጃ አያያዝና ልውውጥ ላይም ፈጣን ለውጥ ያስከትላል፡፡ ቀደም ሲል የነበሩት የቴሌግራምና የቴሌክስ አገልግሎቶች በፋክስና በድረገጽ እንዲለወጡ የቴክኖሎጂ ለውጥ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡ በየቤቱ በመስመር ሽቦ አማካይነት ብቻ አገልግሎት ይሰጡ የነበሩ የስልክ ግንኙነቶች በአሁኑ ጊዜ በተንቀሳቃሽ ስልክ ተተክተዋል፡፡ ይህም ሰዎችን በየትኛውም አካባቢ ወዲያውኑ በማግኘት የሚፈለገውን ተግባር በአጭር ጊዜ ለመፈጸም አስችሏል፡፡



ባለ ሽቦ ስልክ



በኮምፒውተር ኢንተርኔት መጠቀም ይቻላል፡፡



ፋክስ



ተንቀሳቃሽ ስልክ

*ሥዕል 3.17 የመገናኛ መሣሪያዎች*

ኮምፒዩተር መረጃን ለመለዋወጥ፣ ሥራን ለማቀላጠፍ፣ መረጃን ለማጠናቀርና ለማቆየት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ በቴክኖሎጂ መሻሻል ምክንያት በኮምፒዩተሮች ፍጥነት ላይ የሚታየው ለውጥና የመረጃ አያያዝ ብቃት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ነው፡፡ ይልቁንም በየጊዜው በዘርፉ በተደረገው የአሠራር ዘዴ ለውጦች ሰዎች ኮምፒዩተሮቻቸውን በቦርሳቸውና በኪሳቸው ይዘው በመዘዋወር ፈጣን የመረጃ ልውውጥ ማድረግ ችለዋል፡፡

**ተግባር 3.2.9** ☛ ***የጥንድ ሥራ***

**ዓላማ:-** በቴክኖሎጂ ትርጉምና ጥቅም ላይ መወያየት

**መመሪያ:-** በየመቀመጫው ላይ ሁለት ሁለት ሆናችሁ ተወያዩ፡፡

**የመወያያ ጥያቄዎች**

- ቴክኖሎጂ ምን ማለት ነው?
- ቴክኖሎጂ ለግብርናውና ለኢንዱስትሪ ዘርፍ ምን ጥቅም አለው?
- ቴክኖሎጂ የምርት ዕድገትና ጥራት እንዴት ያመጣል?
- ቴክኖሎጂ ለመረጃ ልውውጥና አያያዝ ምን ጥቅም አለው?

በቤት ውስጥ ሥራ ላይ የሚውሉ ምድጃዎች ጭስ አልባ እንዲሆኑ ለማድረግ አዳዲስ ምድጃዎች ጥቅም ላይ ሲውሉ ይታያል፡፡ ብዙዎቹ ምድጃዎች በኤሌክትሪክ የሚሠሩ፣ በቡታ ጋዝ ምግብ ለማብሰል የሚያገለግሉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በአሁኑ ጊዜ በከተሞች በኤሌክትሪክ የሚሠሩ የእንጀራ ምጣዶች በስፋት አገልግሎት ሲሰጡ ይታያሉ፡፡ እነዚህ ምጣዶችም ሆኑ ሌሎች ምድጃዎች ከቴክኖሎጂ ዘርፍ በተገኘ እውቀት የተፈጠሩ ናቸው፡፡ ከእንጨትና ከከሰል ምድጃዎች በጣም የተሻሻሉና ምግብን በንጽሕና ለማብሰል ይጠቅማሉ፡፡ ከዚህም በላይ የምግብ ማዘጋጃ ክፍልን ጽዱና ንጹሕ አድርጎ ለመያዝ ያስችላሉ፡፡ በኤሌክትሪክ የሚሠሩ የቡና መፍጫዎች፣ የሽንኩርት መፍጫዎች፣ ጭማቂ ማዘጋጃዎችና የመሳሰሉት የቀላል ቴክኖሎጂ ውጤቶች ናቸው፡፡

**ተግባር 3.2.10** ☛ *ተግባራዊ ክንውን*

**ዓላማ፡-** በአካባቢያችሁ ከሚገኙ የሱፍ ክሮች ወይንም ተመሳሳይ ክሮች ሹራብ መሥራት

**መመሪያ፡-**ስለ አሠራሩ መጠነኛ ሥልጠና ማግኘት

- የሹራብ ክር ማዘጋጀት
- ሹራቡን መሥሪያ ሽቦዎች ማዘጋጀት

ለጌጣጌጥነት የሚውል የጥልፍ ሥራም ማከናወን ትችላላችሁ፡፡ ጥልፍን ለመሥራት የሚከተሉትን መሣሪያዎች መሟላት አለባችሁ፡፡

- ስለ ጥልፍ መጠነኛ ግንዛቤ የሚያስጨብጥ ጽሑፍ ማግኘት
- የጥልፍ ክር ማዘጋጀት
- የሚጠለፍበት ጨርቅ ማግኘት
- መርፌ ወይም ኪሮሽ ማዘጋጀት

ተማሪዎች እንጨት በመጥረብ፣ ወረቀት በማጣጠፍ ወይም በመቆራረጥ ልዩ ልዩ ቅርጾች ማውጣት ትችላላችሁ፡፡ የመኪና፣ የአውሮፕላን፣ የባቡርና ሌሎች መሰል ቅርጾች መሥራት ትችላላችሁ፡፡

በሠፈራችሁ ልትጫወቱባቸው የምትችሏቸው እንደ ወላንዶ ያሉ ነገሮች ከወረቀት፣ ከእንጨት ወይም ከፕላስቲክ ተረፈ ምርትና ከሲባጎ መሥራት ትችላላችሁ፡፡ ይህ እንቅስቃሴያችሁ ለፈጠራ ሥራ ፍንጭ ስለሚሰጣችሁ መምህራችሁን እየጠየቃችሁና እያሳያችሁ በአካባቢያችሁ ከሚገኙ ቁሳቁስ የተለያዩ ነገሮች ለመሥራት ሞክሩ፡፡

## መልመጃ 3.12

**ሀ. የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ትክክል ካልሆኑ ደግሞ «ሐሰት» በማለት መልሱ፡፡**

1. በሁሉም የአየር ንብረት ክልሎች ግብርና ይካሄዳል፡፡
2. የሰብል ምርት ወተትንና የወተት ተዋጽኦን ያጠቃልላል፡፡
3. አተር የጥራጥሬ ዓይነት ነው፡፡
4. አህያ፣ ፈረስና በቅሎ የቀንድ ከብቶች ናቸው፡፡
5. አርብቶ አደሮች ግመልና ፍየል ያረባሉ፡፡

**ለ. በ"ሀ" ሥር የተዘረዘሩትን በ "ለ" ሥር ከተዘረዘሩት ጋር አዛምዱ።**

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| ______1. በሀገራት መካከል የሚደረግ የምርት ልውውጥ | ሀ. የሀገር ውስጥ ንግድ |
| ______2. የጎጆ ኢንዱስትሪ ውጤት | ለ. የሸክላ ድስት |
| ______3. የግብርና መሣሪያ | ሐ. በቆሎ |
| ______4. የከባድ ኢንዱስትሪ ውጤት | መ. የውጭ ንግድ |
| ______5. ከአካባቢ አካባቢ የሚደረግ የሸቀጣ ሸቀጥ ልውውጥ | ሠ. ማሽላ |
| | ረ. ዶማ |
| | ሰ. ትራክተር |
| | ሸ. ሰሊጥ |
| | ቀ. ምግብ ማቀናበሪያ |

**ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ ሆሄያቱን አክበቡ።**

1. የቀላል ኢንዱስትሪዎች ጥሬ ሀብት የተመሠረተው በምን ላይ ነው?
   ሀ. በግብርና
   ለ. በሸክላ ሥራ
   ሐ. በስጋጃ ሥራ
   መ. በማዕድን ቁፋሮ
2. ከሚከተሉት ውስጥ የከባድ ኢንዱስትሪ ምሳሌ የሆነው የትኛው ነው?
   ሀ. የወረቀት ፋብሪካ
   ለ. የሕትመት ኢንዱስትሪ
   ሐ. የነዳጅ ማጣሪያ
   መ. የምግብ ፋብሪካ
3. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ከባድና ውስብስብ የማምረቻ መሣሪያዎችን ይጠቀማል።
   ሀ. ሲሚንቶ ፋብሪካ
   ለ. ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ
   ሐ. የጫማ ፋብሪካ
   መ. የምግብ ፋብሪካ
4. ከሚከተሉት ውስጥ የቱሪስት መስህብ ያልሆነው የትኛው ነው?
   ሀ. የባሌ ተራራ
   ለ. ጥያ ትክል ድንጋይ
   ሐ. የሐረር ግንብ
   መ. የቀበና ወንዝ
5. ከሚከተሉት ውስጥ ኢትዮጵያ ለውጭ ገበያ የምትልከው ምርት የትኛው ነው?
   ሀ. ሸክላ አፈር
   ለ. ቡና
   ሐ. የግንባታ ድንጋይ
   መ. የወንዝ አሸዋ

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ሀገር የራሷ የሆነ ድንበር፣ ማዕከላዊ መንግሥት፣ ሕዝብና ተፈጥሯዊ ገጽታ ያላት ሉአላዊ ግዛት ናት። ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪካ ከሚገኙ ሀገሮች አንዷ ናት። ኢትዮጵያን ስድስት ሉአላዊ ሀገሮች ያዋስኗታል። እነርሱም ኤርትራ፣ ጂቡቲ፣ ሶማሊያ፣ ኬንያ፣ ደቡብ ሱዳንና ሱዳን ናቸው።

ሀገሮች ከሚኖራቸው ግንኙነቶች በጣም የሚታወቁት ምጣኔ ሀብታዊና ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶች ናቸው።

ኢትዮጵያ ልዩ ልዩ የመሬት ገጽታዎች አሏት። እነዚህ የመሬት ገጽታዎች ከፍተኛ ቦታዎች፣ ዝቅተኛ ቦታዎችና ሸለቆዎች በመባል ይታወቃሉ።

የኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ ከሰሜን ምሥራቅ ወደ ደቡብ ምዕራብ የሚዘረጋ የመሬት ገጽታ ሲሆን በከፍታው በጣም ዝቅተኛ ነው። በኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ ወንዞችና ሐይቆች ይገኛሉ።

በኢትዮጵያ የሚገኙ የውሃ አካላት በወንዞችና በሐይቆች ይከፈላሉ። ታላላቅ ወንዞች በኢትዮጵያ ይገኛሉ። ለምሳሌም ዓባይ፣ ባሮ፣ ተከዜ፣ ዋቢ ሸበሌ፣ ገናሌና ጊቤ ጥቂቶቹ ናቸው። ሐይቆች የከፍተኛና የዝቅተኛ ሥፍራ ሐይቆች ተብለው በሁለት ይከፈላሉ። ከከፍተኛ ሥፍራ ሐይቆች ታዋቂዎቹ ጣና፣ ወንጪና ሐይቅ ናቸው፡፡ የዝቅተኛ ሥፍራ ሐይቆች የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች በመባልም ይታወቃሉ፡፡ ለምሳሌ ዝዋይ፣ ሻላ፣ ላንጋኖ፣ አቢያታና አባያ የመሳሰሉት የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ናቸው።

ኢትዮጵያ የታወቁ በርካታ የዱር እንስሳት አሏት። በኢትዮጵያ ብቻ ከሚገኙ ብርቅዬ የዱር እንስሳት ዋልያ፣ ኒያላና ቀይ ቀበሮ ይገኛሉ።

የኢትዮጵያን ሕዝብ ብዛት ለማወቅ በተለያዩ ጊዜያት የሕዝብ ቆጠራ ተካሂዷል። በተጨማሪም በተለያዩ ጊዜያት የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ትንበያ ተከናውኗል። በ1999 ዓ.ም. የተካሄደው የሕዝብ ቆጠራና በ 2000 ዓ.ም. የተካሄደው የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ትንበያ ግምት በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሥርጭት የተለያየ መሆኑም ይታወቃል። በአንዳንድ አካባቢ በጣም የተጠጋጋ ሲሆን፣ በሌሎች አካባቢዎች መካከለኛና በተቀሩት ደግሞ የተበታተነ ነው። የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በልማት ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ አለው።

በኢትዮጵያ የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴ ግብርና ወሳኝ ሚና ይጫወታል። መጓጓዣና የቴክኖሎጂ ዕድገት ለምጣኔ ሀብት ዕድገት ወሳኝ ነው። መጓጓዣ ለምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ የደም ሥር ነው። የቴክኖሎጂ ዕድገት ለውጥ ለመምጣትና ግብአቶችን ለማሻሻል ከፍተኛ ሚና ይጫወታል።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

### ሀ. የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ትክክል ካልሆኑ ደግሞ «ሐሰት» በማለት መልሱ።

1. ኢትዮጵያን በስተምዕራብ የምታዋስናት ሀገር ሱዳን ናት ።
2. የኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ ከሰሜን ምዕራብ ወደ ደቡብ ምሥራቅ ይዘረጋል።
3. ዝዋይ በኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ ጥልቀት ያለው ሐይቅ ነው።
4. የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ከመሬት ቆዳ ስፋት ጋር የተመጣጠነ መሆን አለበት።
5. በኢትዮጵያ በግብርናው ዘርፍ የሚመረቱት የሰብል ጥራጥሬና የቅባት እህል ምርቶች ናቸው።
6. ባቄላ ከጥራጥሬ እህሎች ውስጥ ይመደባል።
7. ኢንዱስትሪ በኢትዮጵያ ውስጥ  ዋነኛው የምጣኔ ሀብት ዘርፍ ነው።
8. የአዋሽ ብሔራዊ ፓርክ የሚገኘው በላይኛው ስምጥ ሸለቆ ውስጥ ነው።
9. ጣና ሐይቅ የስምጥ ሸለቆ ሐይቅ ነው።
10. ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ለልማት አስፈላጊ ነው።

### ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱን የያዘውን አክብቡ።

1. በኢትዮጵያ ከፍተኛ የሆነው ተራራ ማን ነው?

   ሀ. ባቱ ለ. ካራ ሐ. ራስ ደጀን መ. ኦናሎ

2. ኢትዮጵያን በስተምሥራቅ የምታዋስናት ሀገር ______________ ናት።

   ሀ. ኤርትራ ለ. ሱዳን ሐ. ኬንያ መ. ጅቡቲ

3. የያንጉዲራሳ ብሔራዊ ፓርክ የሚገኘው በየትኛው ክልል ነው?

   ሀ. በአፋር ለ. በአማራ ሐ. በኦሮሚያ መ. በትግራይ

4. ከቅባት እህሎች የማይመደበው የትኛው ነው?

   ሀ. ተልባ ለ. ኑግ ሐ. ሰሊጥ መ. ምስር

5. የሶፍ ዑመር ዋሻ በየትኛው አካባቢ ይገኛል?

   ሀ. በምዕራብ ወለጋ ዞን ሐ. በምሥራቅ ሸዋ ዞን

   ለ. በባሌ ዞን መ. በምዕራብ አርሲ ዞን

**ፍተሻ**

*ልታከናውኗቸው የምትችሏቸውን ተግባራት ለመግለጽ ይህን (✓) ምልክት በሣጥኖች ውስጥ በማኖር አመልክቱ።*

1. የሀገርን ምንነት እገልጻለሁ፣ የኢትዮጵያን መገኛ በአፍሪካ ካርታ ላይ አመለክታለሁ። ☐
2. የኢትዮጵያን የመሬት ገጽታዎችና ዋና ዋና የውሃ አካላትን በመለየት የአንዳንዶቹን ስም እጠቅሳለሁ። ☐
3. በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ ብርቅዬ እንስሳትን ስሞች እጠራለሁ። ☐
4. የኢትዮጵያን ሕዝብ ብዛት በመጥቀስ ሕዝብ ተጠጋግቶና ተበታትኖ የሚኖርባቸውን ክልሎች እለያለሁ። ☐
5. ፈጣን የሕዝብ ቁጥር መጨመር በዕድገት ላይ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ እገልጻለሁ። ☐
6. ግብርናን በሦስት ዓይነት በመክፈል ለሰብል እርሻና ለእንስሳት እርባታ የሚያገለግሉ የታወቁ የእርሻ መሣሪያዎችን እዘረዝራለሁ፣ እጠቀማለሁ። ☐
7. የኢንዱስትሪን ጠቀሜታ በመግለጽና በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋና ኢንዱስትሪዎችን ስሞች በመጥቀስ ኢንዱስትሪዎችን በሦስት ዓይነት እመድባለሁ። ☐
8. የንግድን ጠቀሜታ በመግለጽ የገቢና ወጪ ንግድ ምሳሌዎችን እሰጣለሁ። ☐
9. የቱሪዝምን ጠቀሜታ በማስረዳት በኢትዮጵያ ውስጥ የታወቁ የቱሪስት መስህብ ሥፍራዎችን ስም እጠቅሳለሁ። ☐
10. የቴክኖሎጂን ጠቀሜታ በማስረዳት በኢትዮጵያ ውስጥ እንዴት ጥቅም እንደሚሰጥ ምሳሌዎችን እሰጣለሁ። ☐
11. ቀላል የእጅ (የዕደ ጥበብ) ሥራዎችን ሠርቼ አሳያለሁ። ☐